Qafàr Agatih Rakaakayih Doolatak

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

Qafar Rakaakayak Dinkaara maybalaalaqá

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክርቤትጠባቂነትየወጣአዋጅ

Rakaakayak Malaah Buxa

Teyyeqe kukta

___len sanat____ixximak ----- /2018 I.L.L	Samara____ /2018

Kukti ixxima 155/2018

Qafar Agatih Rakaakayih Doolatak abookiini Ayfaafih roksatih mattaco kee Xiinissô kukta

Aafar agatih rakaakayih doolatal madqah abookiinih xoqoysimak gaaritte yaysennal dacrisoonuh, mexxat leeh xissiime madqah abookiinih ayfaafay yaceenim kee madqah abokiinu kee qadli geyaanamih gaar dacrisoonuh madqah abookiinih ayfaafayitteh meqem kaban caddo fayya haanam faxximtek sah,

Ummattâ tuxxiq dacrisaanam kee qadli dudusaanamih caddol xissiimeh yan ittalluk abit xiinissoh siirat akah baarisak, doolat kee mihratleelah doori hangi kah yaceen meqem kaban xiinissoh siirat xisaanam faxximtaamih taagah;

Abookiini ayfaafayih xaqoysima katayleeh missoyna caabiino le abookiini ayfaafay akah geyan innah xiqsissa abookiini missoyna edde mirracsimtaah, edde xinta siirat baarisaanam faxximteemih taagah,

Rakaakayal abookiini roksat akah yeceen abookaato sittallakleh aydakaanih gitaak kulli

አዋጅ ቁጥር155 /2018

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት በተሻለ ሁኔታ ማስከበር፣ ጥራቱን የጠበቀና የተደራጀ የጥብቅና አገልግሎት አቅርቦት መኖር፣ እና የጥብቅና አግልግሎት የሥነ-ምግባር ደረጃን ማሳደግ የሕግ የበላይነትና ፍትህ የማግኘት መብትን ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የህዝብ ጥቅምን በማስጠበቅና ፍትህን በማስፈን ዙርያ የተደራጀ፤ የመንግስትና የሙያተኞችን ተዋጽኦ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቀጣይነትና ድርጅታዊ ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የጥብቅና ድርጅት የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች በተከታታይ ሥልጠና አማካኝነት በየጊዜው ከሚወጡ

udduerul tawqe rakaakay kee federaalak qusba madqooqiiy, madqa amo gexxa mablooli kee rakaakayaay, baaxo caddo kee baad caddoh ragsit lih edde yamixxigen siirat baarisaanam faxximtek sah,

Qafar agatih rakaakayih doolatak yiysiisen doolat madqak maasayyak 47(3) (A) amakkaquk ciggiltam kuksinte.

Enek-hayto footima

Amolladi

1.Ux ammunta

Ta kukti “abookiini ayfaafayih roksatih mattaco kee xioinisso kuktih ixximak 155/2018” axcuk muggaaqimam xiiqah.

2.Maqnisso

Qangarak afeyti gersi maqna teceeh akke waytek ta kuktih addal: -

1) **“abooke**” yaanam cankah abookiini ayfaafay yacayuh ta kukktak amakkaquk roksat akah yomcowwe num kinni.
2) **"digga le abookiini mihratih ayfaafayih roksat”** yaanam ta kuktal tescessime xiqissoosa kibeh yan numuh yaceen roksat kinni.
3) **"Qiso kiliransi”** yaanam inki abookiini mihratih roksatle num geeh yan culentak qiso mekleh yanim qiso culsa xagar kaak yacee alhum kinni.

የክልሉ እና የፌዴራሉ አዳዲስ ህጎች፣ የህግ ጽንሰ-ሀሳቦች እና ክልላዊ፣ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር የሚተዋወቁበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው ሕገ-መንግስት አንቀፅ 47(3)(ሀ) **መሰረት የሚከተለው ታውጇል፤**

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥ 155 /2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **“ጠበቃ” ማለት የግል የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት ፍቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤**
2) **"የፀና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መስፈርቶች ላሟላ ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤**
3) **"የታክስ ክሊራንስ" ማለት አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሰው ላገኘው ገቢ ግብር ስለመክፈሉ ከግብር አስገቢው አካል የሚሰጥ ማስረጃ ነው፡፡**

4) “**abookiini missoyna**” yaanam ta kuktak amakkaquk abookiini ayfaafay tacayuh xissimteeh, abookiini roksat akah yomcowwe missoyna kinni.

5) **“abookiini mihratih ayfaafay**” yaanam lakqo mekla hiragak hinnay fooca fanah geytima saanih akkek saanih ane sinni tuxxiq geyaanam edde lowwitak hinnay mekla sinnim abooke akkek abookiini missoyna tacee faxe madqah ayfaafay kinnuk ciggiltam addat allele:-

A) adqa caagiidal fayu mattacooy, baatil caagiidaak iroh aban mabbalow taama;

B) Madqa sanadih bicsa akkek maqmiil migaaqal sanad xayyoysaanama;

C) Cokmi buxaaxiiy, xiinisso koboxitteey, garabbih gaar kuriini abbootan le xagortiiy, kal-kaali gaar kuriinih koboxitte kee gersi doorit le daqwat callih gud-gudittel maqmiil awlisak xayyoowaanam kee gaaroowanama.

6) **“Egla”** yaanam ta kuktak maasayyak 57 amakkaquk xissimte Qafar rakaakayak abookeh egla kinni.

7) **“Biiro ”** yaanam kukti ixximak 143/2016 amakkaquk xissimte Qafar rakaakayak qadli biiro kinni.

4) **“የጥብቅና ድርጅት” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመና የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤**

5) **“የጥብቅና ሙያ አገልግሎት” ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም የሕግ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-**

ሀ/ በሕግ ጉዳዮች ላይ ምክር መስጠት፤ ከወንጀል ጉዳዮች ዉጪ የማደራደር ስራ፣

ለ/ የሕግ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም በደንበኛው ስም ሰነድን ማቅረብ፣

ሐ/ በፍርድ ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ጉባዔዎች፣ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባላቸዉ አካላት፤ በግልግል ዳኝነት ጉባዔዎች እና በሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ መድረኮች ደንበኛን ወክሎ መቅረብ እና መከራከር፡፡

6) **“ማኅበር” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 መሠረት የተቋቋመ የአፋር ክልል የጠበቆች ማኅበር ነው፤**

7) **“ቢሮ ” ማለት በክልሉ አስፈጻሚ አካላት እናደገና ማደራጃ እና ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 143/2016 መሰረት የተቋቋመው የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ ነው፤**

8) **“Maqmiil”** Yaanam abookiini ayfaafay hirge num kinni.

9) **“Yasgoorowi”** yaanam abookiini ayfaafay wagsiisa abooke akkek abookiini missoyna kee caagid li asgaarawuk, tiya akkek namma gabuk mekla akkek komishin hirigak hinnay fooca fanah hirgam edde lowwitak maqmiil geysis kee ayseemeniyyal caagid li usuk kaah doore abooke akah yabbixe innah abeh akkek geysiisa faxe num yaanam kinni.

10) **“abookiini taama yasgoorowi gitaak abaanama”** yaanam cokmi buxaaxiiy, gittoyso buxaaxiiy, poliis fanteenaani kee kalah tan qadli xisneena akkek faxe aracal dallaala haysitakl hinnay taamal tan dallaala akkek ummaan qadli xisneenah saqolti akkek taama abeenit lih tuxxiq fantaaxaw ginak abookiini ayfaafay faxeenit abooke fan akkek abookiini missoyna fan akah yameeten innih abto kinni.

11) “**currik yan qabookiini ayfaafay**” yaanam ta kuktak maasayyak 31(1) gubal roorinte abookiini ayfaafay faxeenit kee gersi marih gitaak tanih tan madqooqil tescessime maritte tawwa ta mekla akkek hebelto mekla sinnim abooke akkek abookiini missoyna tacee abookiini ayfaafay kinni.

8) **“ደንበኛ” ማለት የጥብቅና አገልግሎት ተቀባይ ሰው ነው፤**

9) **“አገናኝ” ማለት የጥብቅና አገልግሎትን በሚመለከት ጠበቃን ወይም የጥብቅና ድርጅትን እና ባለጉዳይን በማገናኘት ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ክፍያ ወይም ኮሚሽን በመቀበል ወይም ወደፊት ለመቀበል በማሰብ ባለጉዳዩን በማግባባትና በማሳመን ባለጉዳዩ እርሱ የመረጠለትን ጠበቃ እንዲይዝ የሚያደርግ ወይም የሚያግባባ ማንኛውም ሰው ነው፤**

10) **“የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት” ማለት በፍርድ ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሌሎች የፍትህ ተቋማት ወይም በማንኛውም ስፍራ ደላሎችን በማሰማራት ወይም በተሰማሩ ደላሎች ወይም ከየፍትህ ተቋማቱ ሀላፊዎች ወይም ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች ወደ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እንዲመጡ የማድረግ ተግባር ነው፤**

11) **“ነጻ የጥብቅና አገልግሎት” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 31(1) **ስር ለተዘረዘሩት የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ለተመለከቱ ሰዎች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ያለምንም ክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት ነው፤**

12)“Madqa caagiidah kutbe abe” yaanam abooke akkek abookiini missoynah gubal gacak abooke le gabuuk xayyowta malkititteey, assabaltootiiy, yoo maxioqtaay, waytootaay, radditte kee gersi madqat axaw le sanaditteh missos akkek aysiisuk abooke cata num kinni.

13) “Abooke cateyna” yaanam abooke akkek abookiini missoynah gubat gacak abooke tatteysaah, abookeh madqa mabla missoysaah, bicte malkititteey, assabaltootiiy, yoo maxiqtaay, wayto akkek radditte cokmi buxal akkek gersi madqa numiino le xisneh xaqul geytimak xayyoysaah, wagiitah yan xagar gufsaah, malkit akkek yoo maxiqta maysaqarra faksiisaah, seecissooy, margaqa korraq kee gersi abooke guftam faxximta sanaditte wagiitah yan xagarak hirigak abooke gufsa num kinni.

14) “Maysaqarra” yaanam biiro massossaah, abnookiini roksat akah yeceen abookaato kee abookiini missoynaanih duddale oyta elle yaktuben fidim maysaqarra akkek oyti raceena kinni.

15) “meqem kaban xinta” yaanam abokaato kee abookiini missoynaanih meqem kaban wagsiisak ta kuktak amakkaquk yawqu waa xinta kinni.

12) **“የህግ ጉዳይ ጸሀፊ”** ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ስር በመሆን በጠበቃ በኩል የሚቀርቡ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን፣ መልሶችን እና ሌሎች ህግ ነክ ሰነዶችን በማዘጋጀት ወይም በማረም ጠበቃን የሚያግዝ ሰው ነው፤

13) **“የጠበቃ ረዳት”** ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ስር በመሆን ጠበቃን የሚያማክር፣ ለጠበቃው የህግ አስተያየት የሚያዘጋጅ፣የተዘጋጁ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን ወይም መልሶችን ፍርድ ቤት ወይም በሌላ የህግ ሰውነት ባለው ተቋም ዘንድ በመገኘት የሚያቀርብ፤ ለሚመለከተው አካል የሚያደርስ፣ የክስ ወይም የይግባኝ መዝገብ የሚያስከፍት፤ መጥሪያዎችን፣ የውሳኔ ግልባጮችን እና ሌሎች ለጠበቃው መድረስ ያለባቸውን ሰነዶች ከሚመለከተው አካል በመቀበል ለጠበቃው የሚያደርስ ሰው ነዉ፤

14) **“መዝገብ”** ማለት በቢሮው የሚዘጋጅና የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ የሚመዘገብበት ባህር መዝገብ ወይም የመረጃ ቋት ነው፤

15) **“የሥነ ምግባር ደንብ”** ማለት የጠበቆች እና ጥብቅና ድርጅቶች ሥነ-ምግባርን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፤

16)“**Aydakaakan**” yaanam ta kuktak amakkaquk egla akkek egla mumaxxaga akah tecee xisneh gitaak abokaato taama bagul anuk keenih yaceen madqah aydakaakan kinni.

17)“**Xisne**” yaanam sittallakleh madqah aydakaakan tacee missoyna kinni.

18) “**Boarxi**” yaanam ta kuktak maasayyak 69(1) amakkaquk xissimte abooke xiinissoh boarxi kinni.

19) “**Doolat madqa**” yaanam Qafar agatih rakaakayih doolatih madqa yaanam kinni.

20) “**Rakaakay**” yaanam Qafar agatih rakaaklayih xinto/doolat kinni.

21)“Num” Yaanam gino num akkek madqal numiino gaar akah yeceen xagar kinni.

22)Ta kuktal lab numih nadol xagar kak xaggiime yab say nado addat le.

3. Abbinow waado

Ta kukti biirol abookiini roksat akah yeceen abooke kee abookiini m issoynal abbinow akkele. Nammay-hayto footima Roksat mattacooy, maysaqarra kee aqassaabe

Lani footimak tiya

Roksat mattaco

4.Abookiini roksatih radmoomi

1) Faxe num roksat akah alle kalah

16) **“ስልጠና”** ማለት በዚህ አዋጅ መስረት በማህበሩ ወይም ማህበሩ እውቅና በሰጠው ተቋም አማካኝነት ለጠበቆች በስራ ላይ እያለ የሚሰጥ የህግ ስልጠና ነዉ፤

17) **“ተቋም”** ማለት ተከታታይ የህግ ስልጠና የሚሰጥ ድርጅት ነዉ፤

18) **“ቦርድ”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69(1) መሠረት የተቋቋመ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ነው፤

19) **“ሕገ መንግስት”** ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት ነው፤

20) **“ክልል”** ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር/መንግስት ነው፤

21) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

22) በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በቢሮው የጥብቅና ፈቃድ በተሰጠው ጠበቃ እና የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>ስለ ፍቃድ አሰጣጥ፤ ምዝገባ እና እድሳት</u>
<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
<u>ስለ ፍቃድ አሰጣጥ</u>

4. <u>የጥብቅና ፍቃድ መርሆዎች</u>

1) ማንኛዉም ሰዉ ፍቃድ ሳይኖረዉ

abookiini ayfaafay yaceem maxiiqa;

2) Abookiini roksat rakaakayal maytani taama le numuh mayam-cawwa,

3) Faxe abookiini roksat geyam faxa num ta kuktal wannowte xiqissoosa kibam faxximta.

4) Ta maasayyak lani maasayyak 2 elle daccarsime innal elle anuk, faxe num nadooy, diiniiy, afaay, samad akkek ayyuntiino mamaataay, siyaasa mablaay, ikoytaay, ubukyaay, xagar erkenna akkek faxe toobisle caalat rakiibo abak roksat kaah makalitan.

5.Roksat elle faxxiima caalat:-

Ciggilta xagorti abookiini roksat keenik faxxiime kalah abookiini ayfaafay yaceenim xiiqaanah:-

1) Isi caagidih gaaroowa num;

2) Mekla sinni sinnim rahim wadaytuuy, isi xaleenaay, isi baxah, isi kaxxa abbah, isi maqanxah, iisi toobokoytah isi rahimih wadaytih xaltaniiy, tonnah yaynabi akkek qarseena kaak yekke numuh gaaroowa num,

3) Taamat axawah yan caagidih gaaroowa gaaroyse,

4) Gaanuun numiino le kabxa missoynaay, siviil ayyuntih massoynaay, ummattta missoynaay, diini xisneey, mihrat eglaay, baad caddoh missoyna akkek gersi gitaliino le madqak amakkaquk xissimte

የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

2) **የጥብቅና ፍቃድ በክልሉ ውስጥ ቋሚ ሥራ ላለው ሰው አይሰጥም፤**

3) **ማንኛዉም የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰዉ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤**

4) **የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰዉ በጾታ፤ በሀይማኖት፤ በቋንቋ፤ በዘር ወይም በማህበራዊ አመጣጡ፤በፖለቲካ አመለካከቱ፤ በንብረቱ፤ በትዉልዱ፤ በአካል ጉዳት ወይም ማንኛዉንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ፍቃድ አይከለከልም፡፡**

5. <u>ፍቃድ የማያስፈልግበት ሁኔታ</u>

የሚከተሉት አካላት የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልጋቸዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡-

1) **ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰዉ፤**

2) **ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛዉ፤ ለወላጁ፤ ለልጁ፤ለአያቱ፤ለእህቱ፤ለወንድሙ፤ለትዳር ጓደኛዉ ወላጆች፤ እንዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰዉ የሚከራከር ሰዉ፣**

3) **ከስራዉ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር ዐቃቤ ህግ፣**

4) **ሕጋዊ ሰውነት ባለው የንግድ ድርጅት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፤ ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማህበር፣ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም በሌላ አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፣**

missoynat tamlimak awlime num,

5) Doolat maktab akkek daddos missoyna wagsiisak gaarow aba faxe doolat maktab akkek daddos missoynah abbootan li akkek saqal hinnay usuk awlise num hinnay,

6) Faxe taama abeenit eglah mirac akkek egla awlisse num.

6.Roksat geyoonuh kibaanam faxximta xiqissoosa

1) Faxe abookiini mihratal gacam faxa num abookiini roksat geyuh, ciggilta xiqissoosa kibam kaak faxxiimele: -

A) Itiyoppiyah agat baxiino le hinnay Itiyoppiyal ubka abe num,

B) Mumaxxaga le Itiyoppiyak fayyale barittoh xisnek dagnal madqal dimloom le num,

C) Illacaboh uddur edde taamitak suge xisnek, ta missoyna cabak afat yan namma sanootah addat qilsi ossobba qellatah diggilime weeh, meqeh yan meqem kaban arcisso xayyoysam xiiqa num,

D) Madqa mihratal faxxiimah yan taamah abak raag kibaah, faxximteh tenek roksat geyuh yaceen mihrat culmah aqayyaarel tatreeh,

E) Rakaakayak taamah afat yaabam xiiqa num.

2) Ta maasayyak lani maasayyak

፤

5) የመንግስት መስርያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛዉም የመንግስት መስርያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሀላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰዉ፣ ወይም

6) ማንኛዉም የሰራተኛ ማህበር መሪ ወይም ማህበሩ የሚወክለዉ ሰዉ።።

6. ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) ማንኛዉም በጥብቅና ሙያ መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለዉ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ በህግ ዲፕሎማ ያለዉ፣

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና የመልካም ስነምግባር ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

መ) በህግ ሙያ የሚፈለገዉን የስራ ልምድ ያሟላ እና እንደአስፈላጊነቱ ፍቃድ ለማግኘት የሚሰጠዉን የሙያ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣ እና

ሠ/ የክልሉን የሥራ ቋንቋ መናገር የሚችል።።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተዉ ቢኖርም ከኢትዮጵያ ዉጪ ካለ ዕዉቅና ካለዉ

1(b) tescesasimem anih, ityoppiyak iroh tan mamaxxaga leh tan fayyale caddoh barittoh buxaaxil madqal qimboh xigri geeh yan faxe num kee maasayyak 12(2), 13(2) kee 14(2) gubal tescessime xqisoosa kibta kaa tekkek abookiini roksat kaah yaceenim xiiqaanah.

3) Ta maasayyak 1 al tescessimeh tan xiqisoosa kibtah yan faxe num, faxximta sanaditte luk, abookiini rosatih assabalta Rakaakay Qadli Biirol xayyoysam faxximta;

4) Ta maasayyak lani maasayyak 1(d) amakkaquk xayyowta aqayyaareh xaloot melleb yallu xiiqam, ta xali edde yewqeh yan ayrok xabba haanam inki sanatih addat xayyooweh yenek dubuk kinni.

7.Roksat akah acee waan sababitte

Faxe numuh abookiini roksat akah acee waanam:-

1) Ta kuktak maasayyak 6 lani maasayyak 1al tesessime xiqsoosa kibe weeh yenek;

2) Acsabuk yagdubeenim kee mihrat meqem kabanih nakusi lih axaw luk sidiica sanat kee tohuuk daga diggale axaw digalsissa baatilih maltimak

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ የተሰጠዉ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(2)፣ 13(2) እና 14(2) ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል

3) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻውን ለክልሉፍትህ ቢሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤**

4) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) መሰረት የሚቀርበዉ የፈተና ውጤት ዋጋ የሚኖረዉ ውጤቱ በታወቀ በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥ ከቀረበ ብቻ ነዉ።።**

7. <u>ፍቃድ የማያሰጡ ምክንያቶች</u>

ማንኛዉም ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ የማይሰጠው፡-

1) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፤**

2) **ታስቦ በሚፈፀምና ከሙያ ስነምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና**

qellat deqsiteeh, gitaliino le madqal muggaaqime weeh yenek,

3) Madqah ayfaafayal akah gace waa innah madqal hinnay cokmi buxal waasimeh yenek kinni.

8. Roksat mattacayyo/mattaco

1) Ta kuktak amakkaquk rakaakay abookiinih roksat tacee abookiini roksatih agaaradih makaadoh margaqak abakkaquk maktab kinni.

2) Yassaballi ta kuktak maasayyak 6 (3) amakkaquk kibnele assabalta edde xayyoyse udduruk xabba haanam 30 ayroh addat abookiini roksatih agaaradih makaado faxximtah akak inta margaqa taceem faxximta.

3) Abookiini roksatih assabalta oggol gee waytek abookiini roksartih agaaradih makaado margaqa rakiibo abak maktab assabalta oggol akah gee wayte sabab makaado margaqa edde yeexege uddurуuk 10 takke taamah ayroora kutbeh yassaballi taysixxigem faxximta.

4) Abookiini roksatih agaaradih makaado ta maasayyak lani maasayyak 1 amakkaquk roksat yacayoonuh madqeenik, 15 takke taamah ayroorah addat abookiini roksat yassaballih biro gitaak yaceenim faxximta.

5) Abookiini ayfaafay edde yaceen

አግባብነት ባለው ህግ ያልተሰየመ ከሆነ፤

3) በሕግ አገለግሎት እንዳይሰማራ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ከሆነ ነው፡፡

8. ፍቃድ ስለመስጠት

1) በዚህ አዋጅ መሰረት **የክልል የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጠዉ** በጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ ዉሳኔ መሰረት በቢሮው ነዉ፤

2) አመልካቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(3) መሰረት የተሟላ ማመልከቻ ባቀረበ በ30 ቀናት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ ተገቢ የሚለዉን ዉሳኔ መስጠት አለበት፤

3) የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ የጥብቅና ፈቃድ ግምጋሚ ኮሚቴዉን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ በቢሮው ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት የኮሚቴዉን ዉሳኔ ባወቀ በ10 የስራ ቀናት ዉስጥ በጽሁፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፤

4) የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍቃድ እንዲሰጥ ከወሰነ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃዱን ለአመልካቹ በቢሮው በኩል መስጠት አለበት፤

5) የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜ

uddur roast gatbaral baxxaqisaanam faxximta ximmoomah rorti biro tayyaaqu wayta miracsental akah madqimele.

6) Abookiini roksatih agaaradih makaado assabalta radim abeenik yassaballi assabalta radim abeenim edde yeexege uddurуuk ugutak 15 takke taamah ayroorah addat weeqa borxil xayyoysam xiiqah.

7) Borxi margaqal weeqa le xagar margaqa korraq kaa edde gufte uddurуuk qembisak tanih tan 30 ayroorah addat yoo maxiqta rakaakayak fayyale cokmih buxal xayyoysam xiiqah.

9.Xiiba kori agdaabe

Xiiba kora aba num kibaal oggoluh aboonuh xiiqan rakiibo milaagitte elle daccarsinte innal elle anuk, faxe abookiini ayfaafayih roksat akah yaceen abooke ciggilta xiiba kora kutbeh diggoysa:-

«Anu---------- asaaku---------- ayro----------I.L. L Qafar rakaakayak abookiini roksat hirga wak rakaakay kee baaxok doolat dastuur kee madqooqi assakaxxuh, askaxxuh qadli siiratih farmo arcisuh meqeh yan meqem kabanal inni mihrat naaho maqaane kee aamantiinol taamituh awlisu waah an inni maqmilwah tuxxiq madqa elle idnissa gurral askaxxuh, gaarow abeenit kee mihrat wadaytit lih bicak askaxxuk taamituh, liyoh an ixxiga kee duddal madqa daga raaqiyyal faxxiimah yan cato abuh xagana cula".

በፍቃድ ደብተር ላይ መጠቀስ ያለባቸዉ ነጥቦች ዝርዝር በቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

6) የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴዉ ማመልከቻዉን ዉድቅ ካደረገዉ አመልካቹ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፤

7) በቦርዱ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ወገን የውሳኔ ግልባጭ ከደረሰዉ ጊዜ ጀምሮ ባለ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

9. <u>ቃለ መሀላ ስለማስፈጸም</u>

የቃለ መሀላ ፈጻሚዉን ዕምነት ለማስተናገድ ሊደረጉ የሚችሉ ምክንያታዊ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛዉም የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ የሚሰጠዉ ጠበቃ የሚከተለዉን ቃለ መሀላ በጽሁፍ ያረጋግጣል፡-

«እኔ _____ዛሬ_____ቀን___ ___ዓ.ም የአፋር ክልል የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል የክልሉንና የሀገሪቱን ህገ-መንግስት እና ህጎች ላከብር እና ላስከብር፤ ለፍትህ ስርዐአቱ ተልዕኮ መሳካት በመልካም ስነ-ምግባር በሙያዬ በቅንነት እና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸዉን ደንበኞቼን ጥቅም ህግ በሚፈቅደዉ አግባብ ላስከብር፤ ከተከራካሪዎቼ እና የሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት እና በመከባበር ልሰራ እና፤ ባለኝ እዉቀት እና ችሎታ ለህግ የበላይነት ተገቢዉን ዕገዛ ለማድረግ ቃል እገባለሁ»

10. Abookiini roksatih qaynatitte

Rakaakayak abookiini roksatih qaynatitte:-

1) Daqar cokmih buxa akkek magaalak qembo caddoh cokmih buxak abookiini roksat;
2) Faxe cokmih buxah abookiinih roksat kee
3) Baxsale abookiini roksat kinnon.

11. Daqar cokmih buxa akkek magaalak qembo caddoh cokmih buxah abookiinih roksat

1) Ciggilta tan shartitte kibta Faxe Itiyoppiyah xaylo hinnay Itiyoppiyal yooboke num daqaarak cokmih buxa hinnay magaalak qembo caddoh cokmih buxak madqâ cokmih buxal abookiini roksat kaah amcawwele:

A. Itiyoppiyak mamaxxaga leh tan fayyale caddoh barittoh buxak madqak barittol naharsi degree leeh, gaanun mihratiinul dagnal namma sanatih taamah abak raag le; hinnay madqal diploma kee affara sanatih taamah madqa mihratiinih abak raag le num;
B. Caddol yaceen abookiini roksatak culmah aqayyaarel tatrek,
C. usuk/is ellecabo elle taamitak sugte

10. <u>የጥብቅና ፍቃድ አይነቶች</u>

የክልል የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች፡-

1) የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣
2) የማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣ እና
3) ልዩ ጥብቅና ፈቃድ፤

ናቸው፡፡

11. የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣

1) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የወረዳ ፍርድ ወይም የከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

ሀ) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ የመጀመርያ ዲግሪ የተመረቀ እና በህግ ሙያ ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ፤ ወይም በህግ በዲፕሎማ የተመረቀ እና በህግ ሙያ አራት አመት የስራ ልምድ ያለዉ፣

ለ) ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት

massoyna cabak naharal namma sanatih addat gibdi ossobba baatilih digaalime weeh,

D. Nagay yan meqem kaban leemil arcisso xayyoysam xiiqa num.

12. Faxe cokmih buxah abookiinih roksat

Tahaak gubal tan xiqissoosa kibta Faxe Itiyoppiyaytu hinnay Itiyoppiyal yooboke num rakaakay faxe cokmih buxal abookiini roksat kaah amcawwele.

A) Itiyoppiyak mamaxxaga leh tan fayyale caddoh barittok buxak madqâ barittol naharsi degree kee madqâ mihratal dagnal affara sanatih abak raag le num, hinnay gaanun madqa barittok xiploma kee 6 sanatih taamah abak raag leh yan numuh;

B) Faxxinte kaa tekkek ta caddoh yaceen abookiini roksatigh culmah aqayyaarek tatrek,

C) Illecabo elle taamitak suge massoyna cabak naharal namma sanatih addat gibdi ossobbai qellatah digaalime weeh;

D) Nagay yan meqem kaban leemil arcisso xayyoysam xiiqa num.

13. Baxsale abookiini roksat

Baxsale abookiini roksat: -

1) Rakaakay ayyuntah amolladi gaar kee tuxxiiq dacrisoonuh currik madqâ ayfaafah akah yamcawwe num ciggiltah tan xiqsissoosa kibah yan numuh

ባለት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና

መ) መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

12. <u>የማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የክልል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

ሀ) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ እና በህግ ሙያ ቢያንስ የአራት ዓመት ልምድ ያለው ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ እና በሕግ ሙያ ስድስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና ፍቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት ባለት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና

መ) መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

13. <u>ልዩ የጥብቅና ፍቃድ</u>

ልዩ የጥብቅና ፍቃድ፡-

1) በክልሉ የሕብረተሰቡን አጠቃላይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በነጻ የህግ አገልግሎት ለሚሰጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች ለሚያሟላ

baxsale abookiini roksat amcawwele:-

A) Mamaxxaga geyte fayyale barittoh xisne madqal qembo caddoh digri leeh mihratal dagnal affara sanat yoyfoofeh akkek madqal diploomuk dooqaysimeeh, mihratal dagnal 6 sanat yoyfoofeh akkek mumaxxaga geyte fayyale baritto xisnek madqal qembo caddh digri leeh mihratal dagnal affara sanat yoyfoofeh akkek madqal diploomuk dooqaysimeeh, mihratal dagnal 6 snanat yoyfoofe mihratli le xisne akkek missoyna

B) Awlisah yan ayyunti exxa aw maqmiilik lakqo hirge waah,

C) Meqeh yan meqem kaban lem diggossa alhum wagiitah yan xagarak xayyoysam xiiqa num.

2) Faxe rakaakayak abookiini roksat leh yan num baxsale abookiini roksat faxsiise kalah baxsale abookiini ayfaafay yaceem xiiqah, laakin ta ayfaafay yaceek afal biiro kutbeh yaysixxigem faxximta.

3) Baxsale abookiini roksat akah yeceen num akkek missoyna abookiini ayfaf yacee wak, ta kukta kee abooke meqem kabanih xinta katayta gurral yagdubem faxximta.

14. Madqa barseenitih yaceen abookiini roksat.

1) Ta kuktak maasayyak 4(2) gubal wannowtem anih fayyale baritto xisneena madqa barittoh buxaaxil

ሰው ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፡-

ሀ) ዕዉቅና ካገኘ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ አራት አመት ያገለገለ ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀና በሙያው ቢያንስ 6 ዓመት ያገለገለ፣ ወይም ዕዉቅና ካገኘ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ አራት አመት ያገለገለ ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀና እና በሙያው ቢያንስ 6 ዓመት ያገለገለ ባለሙያ ያለው ተቋም ወይም ድርጅት ፣

ለ) ከሚወክለዉ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ደንበኛ ክፍያ የማይቀበል፤ እና

ሐ) መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተዉ አካል ማቅረብ የሚችል፡፡

2) **ማንኛዉም የክልሉ ጥብቅና ፍቃድ ያለዉ ሰዉ ልዩ የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልገዉ የልዩ ጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላል፤ ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ለቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤**

3) **ልዩ የጥብቅና ፍቃድ የተሰጠዉ ሰዉ ወይም ድርጅት የጥብቅና አገልግሎቱን ሲሰጥ ይህን አዋጅ እና የጠበቃ ስነምግባር ደንብን በተከተለ መልኩ መፈጸም አለበት፡፡**

14. <u>ለሕግ መምህራን ስለሚሰጥ የጥብቅና ፍቃድ</u>

1) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 4(2) **ስር የተደነገገዉ ቢኖርም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሕግ መምህር**

barisa , ityoppiyah baxa akkek ityoppiyal yooboke madqa barseeni maasayyak 12(1) hinnay maasayyak 13(1) il yeceenim kibe kaa tekkek madqa barsiyyih mihrat cabam faxsiise kalah abookiini roksat kaah yaceenim xiiqaanah.

2) Ta maasayyak lani maasayyak 1 ugutak, abookiini mihratih ayfaafay madqâ barittoh buxah barseenah yaceen wak, abookiini taama bartiyya kee barsiyyi taamah gexsit agaaguluse waytam barseeni elle barisa xisnek arcisaanam faxximta.

15. Abookiini mihratak culmah aqayyaare wagsiisak

1) Ta kuktak maasayyak 6(1) gubal wannowtem kibe faxe abookiini ayfaafayal gacam faxa num abookiini mihratak cuklmah aqayyaare beyam kaak faxximta.

2) Ta maasayyak lani maasayyak (1) wannowtem anih, madqal qembo caddoh digri leeh, ltiyoppiyal geytimta fayyale baritto xisneenah addal madqa barsiyyal koona sanat yoyfoofeeh, gaar kuriinooy, gaaroysiinuuy, doolat maktab akkek doolatak daddos missoynah addat madqa fayu abe akkek madqa mihratlih, aw calloyse akkuk dagna affara sanat yoyfoofeeh, cattiimiyyi

በአንቀጽ 12(1) ወይም በአንቀጽ 13(1) ላይ የተጠቀሰዉን ካሚላ የህግ መምህርነት ሙያውን መልቀቅ ሳያስፈልገው የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል፤

2) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለሕግ ትምህርት ቤት መምህር ሲሰጥ የጥብቅና ሥራው የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል ስለመሆኑ መምህሩ የሚያስተምርበት ተቋም ማረጋገጥ አለበት፡፡**

15. <u>ስለ ጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና</u>

1) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) ስር የተደነገጉትን የሚያሟላ ማንኛዉም በጥብቅና አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና መዉሰድ ይኖርበታል፤**

2) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ኖሮት በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በህግ መምህርነት ለአምስት ዓመት ያገለገለ፤ በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ በህግ አማካሪነት ወይም በህግ ባለሙያነት ወይም በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአራት ዓመት ያገለገለ፤ በረዳት ዳኝነት፣ በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት የህግ ጉዳይ ፀሐፊነት ወይም የጠበቃ ረዳትነት እንዲሁም**

gaar kuriinu akkek abooke akkek abookiini missoynat madqa caagiidah kutbe akkek abooke cateynah tonnah siviil ayyuntih missoynat, diini xisneenal, baad caddoh missoynaaniiy, kabxa misoynaani kee gersi xisneenal madqa fayu abe akkuk hinnay, madqa mihratiinu akkek calloyse akkuk dagnal laca sanat yoyfoofe Itiyoopiyah baxa akkek Itiyoppiyal yooboke num taama edde cabe udduruk inki sanatih addat abookiini roksatih assabalta xayyoyseh yenek, abookiini roksat aqayyaare sinnim kaah yaceenim xiqqimtah.

3) Maktab abookiini roksatih agaaradih makaado roksat akah yaceen innah akah madqen mihratlih abookiini roksat aceele.

16. Abookiini roksatih maysaasa wagsiisak

1) Rakaakayal daqar cokmih buxal hinnay magaalak naharsi caddol abookiini roksat geeh yan abooke, taamah abak raag hinnay barittô caddol roksat kaah yaceen ken tekkek caddo kaah yaysiisoonuh maktabal assabaltah esseram xiiqah.
2) Ta maasayyak 1hayto maasayyak wannottem anih, rakaakayak daqar cokmih buxal hinnay magaalâ qembo caddoh cokmih buxak abookiini roksat

በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ በሀይማኖት ተቋማት፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በንግድ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት በህግ አማካሪነት ወይም በህግ ባለሙያነት ወይም በነገረፈጅነት ቢያንስ ለስድስት ዓመት ያገለገለ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ የጥብቅና ፍቃድ ያለፈተና ሊሰጠው ይችላል፤

3) ቢሮው የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ፈቃድ እንዲሰጠዉ ለወሰነለት ባለሙያ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤

16. የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ ስለማሻሻል

1. በክልሉ የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ጥብቅና ፍቃድ ያለው ጠበቃ የስራ ልምዱ ወይም የትምህርት ደረጃው ፈቃድ የሚያሰጠው ከሆነ ደረጃው እንዲሻሻልለት ለቢሮው ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ተደነገገው ቢኖርም በክልሉ የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥብቅና ፈቃድ ያለው ጠበቃ

le abooke madqal qembo caddoh digri yelleeh, abookiini roksatal affara sanat, tonnah madqal diploom yelleeh, abookiini roksatal laca sanat yoyfoofeh yenek, abookiini ayfaafayih taama cabe kalah rakaakayak faxe cokmih buxal abookiini roksat aqayyaare maleh kaah yaceenim xiqqimtah.

Lani footimak nammaya.

Maysaqarra kee aqassaabe

17. Maysaqarra

1)Biiro abookiini roksat akah tecee abookaato kee abookiini missoynaani inkih yan alhum qasriino le gitah yaktubeenim faxximta.

2)Maysaqarra siiratih addat gactu wayta rorti ximmooma biiro tayyaaqu wayta miracsental akah madqimele.

3)Biiro ta maasayyak lani maasayyak 1 amakkaquk qusbih yuktuben abnookaato kee abookiini missoynaanik migaq rorta kulli sidiica alsal egla yaysixxigeenim faxximta.

4)Biiro abookiini roksat akah tecee abookaato kee abookiini missoynaanih alhum ayyunta akah gufta innah baxaa-baxsale gitah aysixxigele.

18.Abookek akkek abookiini missoyna lih takke taamoomi

1) Faxe abooke hinnay abookiini missoynak madqa caaghiidah kutbe abeenaay,

በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለአራት ዓመት እንዲሁም በህግ ዲፕሎማ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለስድስት ዓመት ካገለገለ የጥብቅና አገልግሎት ሥራውን ሳይተው የክልሉ ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ያለፈተና ሊሰጠው ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት
ምዝገባ እና እድሳት

17. ምዝገባ

1) ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ ዘመናዊ በሆነ መንገድ መመዝገብ አለበት፤

2) በምዝገባ ስርዓቱ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነጥቦች ቢሮው በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፤

3) ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አዲስ የመዘገባቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ስም ዝርዝር በየሶስት ወሩ ለማህበሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

4) ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች መረጃ ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በተለያየ መንገድ ይፋ ያደርጋል፡፡

18. ከጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ጋር ስለሚሰሩ ሰዎች

1) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት

abooke cateyna hinnay gersi taamah faxximta taama abeynit tamlisam duudaah, abookiini missoyna tama galab akak xaggiime taama abeenitit ossotinah abooke tamlisam xiiqah.

2) Ta maasayyak lani maasayyak 1 amakkaquk tamlo abe abooke akkek abookiini missoyna tamlo edde tekke waktiik namma alsitteh addat tamlise numuk duddale alhum biiro yaysixxigeeh yasqarrem/yaktubusem faxximta.

3) Faxe abooke akkek abookiini missoyna ciggilta madqa caagiidah kutbe abeena akkek abooke cattiime tamlissam maxiqta:-

   A) Abooki roksat akak waasimeh akkek akak duugume num;

   B) Migaq maysaqarrak akak duugume num

   C) Biirok ossobba qellatah xiiriyime num;

   D) Meqem kabanat axawah yan baatilih malkitimeeh diggalsimeeh, muggaaqime wee num akkek;

   E) Maytani taama le num;

   F) Madqa baritto akkek madqa mihratal abak raag alle waa num.

19. Roksat aqusbusiyya wagsiisak

1) Abookiini roksat kulli sanatal abinal edde ase illacaboh ayrook qembisak ainki alsa yakke waktih addat yaqussubem faxximta.

የህግ ጉዳይ ጸሀፊ፣ የጠበቃ ረዳት ወይም ሌሎች ለስራዉ የሚያስፈልጉ ሰራተኞችን መቅጠር የሚችል ሲሆን የጥብቅና ድርጅት ከነዚህ ከተጠቀሱት ሰራተኞች በተጨማሪ ጠበቃ ሊቀጥር ይችላል፣

2) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቅጥር የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ቅጥሩ በተፈጸመ በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ ሥለተቀጠረው ሰው ሙሉ መረጃ ለቢሮው ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፣**

3) **ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉትን በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት ወይም በጠበቃ ረዳትነት መቅጠር አይችልም፡-**

   ሀ) የጥብቅና ፍቃዱ የታገደን ወይም የተሰረዘን ሰው፣

   ለ) ስሙ ከመዝገብ የተፋቀን ሰው፣

   ሐ) ከቢሮው በዲሲፕሊን ጥፋት የተባረረን ሰው፣

   መ) ከስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ እና ያልተሰየመን ሰው፣ ወይም

   ሠ) ቋሚ ስራ ያለዉን ሰው፣

   ረ) የሕግ ትምህርት ወይም በህግ ሙያ የስራ ልምድ የሌለዉን ሰው፡፡

19. <u>ስለፍቃድ እድሳት</u>

1) **የጥብቅና ፍቃድ በየዓመቱ ፍቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በአንድ**

2) Faxe abooke akkek abookiini missoyna ta maasayyak lani maasayyak 1 al galab akak xaggiimem waktih addat roksat aqusbnuse kal raaqek ciggiila inki alsih addat biro tayyaaqu wayta miracsentak amakkaquk kaal radeh yan lakqo digaala mekelak roksat kaah aqussubele.

3) Abooke hinnay abookiini missoyna ta maasayyak lani maasayyak (2) wannoowe waktih waadoh addat isi roksat yaqusbuseenim akah duude weem kay lowsiisik iroh tan sababitteh tekkem kinnim elle yayseemene xiiqa alhum xayyoyse kaa tekkek biiro tayyaaqu wayta miracsentak amakkaquk kaal qidoonu waan digaala mekella heeh ciggiila inki alsa yakke wsaktih addat abookiini roksat yaqusbusem xiiqah.

4) Faxe abooke akkek abookiini missoyna ta maasayyak amakkaquk roksat yuqusbuse week, ossobba malkit kaak xayyoowele.

20. Roksat yaqusbusoonuh xayyoysan alhumitte;

Faxe abooke akkek abookiini missoyna abookiini roksat yaqusbusoonuh xciggita alhumitte xayyoysaanam keenik qambalsimta:-

1) Qiso kiliransi;

ወር ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፤

2) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ በሚቀጥለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ቢሮው በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ ፍቃዱ ይታደስለታል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠበቃዉ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ፍቃዱን ያላሳደሰዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ ቢሮው በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፍቃዱ ሊታደስለት ይችላል፤

4) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ መሰረት ፍቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ የዲሲፕሊን ክስ ይቀርብበታል፡፡

20. <u>ፍቃድ ለማሳደስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች</u>

ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃድን ለማሳደስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1) የታክስ ክሊራንስ፤

2) Ta kuktak maasayyak 30(4) amakkaquk dirkissa madqah aydakaakan akah yeyxeeren abooke akke waytek ta kuktal daffeyte aydakaakan dirkik gaba kalem qaddoysa alhum;

3) Abookaatoh eglah meklam kaak qambalsinta adoytiini ufya meklem kaah arcissa egla kaah tacee alhum;

4) Karma akak 70 sanataak daga akak gufte abooke gaanuuniyyat le qaafiyat xisnek abookiini ayfaafay yacayuh kaa xiqsissa qaafiyat caalatal yanim qaddossa alhum kee

5) Sanat addat yaceem kaak qambalsinta currik tan abookiini ayfaafay yeceem kaah arcissa alhum.

21.Roksat mattaco

1) Faxe abooke ciggilta caaloota kaa matarta wak, abookiini roksat biiroh gacisam faxximta:-

A) Mihrataak iroh tan taamal maytanih taamitak geytima kaa tekkek,

B) Abookiini ayfaafay yaceem xiiqe waa kaa tekkek,

C) Abookiini ayfaafay soolisam faxeh yenek,

2) Ta maasayyak lani maasayyak 1 amakkaquk abooke roksat gacisuh yassubulle wak, biiro abookiini roksatih gatbara saanih tabissam

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30(4) መሰርት አስገዳጅ የህግ ስልጠና ከተራዘመለት ጠበቃ በስተቀር ጠበቃዉ በዚህ አዋጅ የተቀመጠዉን የስልጠና ግዴታ ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፤

3) ለጠበቆች ማህበር መክፈል የሚጠበቅበትን የአባልነት መዋጮ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ከማህበሩ የሚሰጥ ማስረጃ፤

4) እድሜዉ ከ70 አመት በላይ የሆነ ጠበቃ ህጋዊ ከሆነ የጤና ተቋም የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ ያለ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ፤እና

5) በዓመት ዉስጥ መስጠት የሚጠበቅበትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ስለመስጠቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

21. <u>ፍቃድን ስለመመለስ</u>

1) ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የጥብቅና ፈቃዱን ለቢሮው መመለስ አለበት፡-

ሀ) ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በቋሚነት የተሰማራ እንደሆነ፣

ለ) የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፣

ሐ) የጥብቅና አገልግሎት ለማቆም ከወሰነ።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ጠበቃዉ ፍቃድ ለመመለስ ሲያመለክት ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ ደብተሩን ወዲያዉኑ መረከብ አለበት፣ ሆኖም

faxximta. Laakin abookiini ayfaafay yirgiqem qaddoysa alhum abookeh yaceenim abooke wagiitah yan xagarak qiso kiliransi luk xayyoowa waka,

3) Ta maasayyak lani maasayyak 1 amakkaquk roksat gacise abooke abookiini taama fan yadaarem faxek, roksat qagitak beetam xiiqah, laakin abooke abokiini ayfaafayak namma sanataak dagah baxsimeh sugeeh, madqa mihratak iroh tan taamal gaceh sugek, roksat kaah yaduurem caddoh yaceen abookiini culmah aqayyaare beeh tatra waka.

Sidoc-hayto footima

Abookaatok mihrat dirki

Lani footimak tiya

Amolladi abokaath dirki

22. Abookiini roksatat axaw le dirki

Faxe abooke akkek abookiini missoyna:-

1) Maqmiiliy, cokmi buxa akkek faxe gitaliino le xagar abookiini roksat akah yayballe innah kaal esseran wak, yaybulleemih dirki kaal tan.
2) Abookiini roksat faxe caalatal gersi marih xaqoysim akkek mayfaafah tatruseh yaceem kaak mafaxximta.

23. Abookiini ayfaafayak ambalal kee tohut axaw le dirkitte

ı) Faxe abooke akkek abookiini missoyna ux waktih addat yaceen madqa fayih

የጥብቅና አገልግሎቱን ማቋረጡን የሚገልጽ ማስረጃ ለጠበቃዉ የሚሰጠዉ ጠበቃዉ ከሚመለከተዉ አካል የግብር ክሊራንስ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፤

3) **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፍቃዱን የመለሰ ጠበቃ ወደ ጥብቅና ስራው መመለስ ከፈለገ ፍቃዱን መልሶ ሊወስድ ይችላል፣ ሆኖም ጠበቃው ከጥብቅና አገልግሎቱ ከሁለት ዓመት በላይ ተለይቶ የቆየው ከህግ ሙያ ውጪ በሆነ ስራ ላይ ተሰማርቶ ከሆነ ፍቃዱ የሚመለስለት ለደረጃዉ የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ወስዶ ካለፈ ብቻ ነው፤**

ክፍል ሶስት

የጠበቆች የሙያ ግዴታ

ንዑስ ክፍል አንድ

ጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ

22. ከጥብቅና ፍቃድ ጋር የተያያዘ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1) **በደንበኛ፣ በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው አካል የጥብቅና ፍቃድን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤**

2) **የጥብቅና ፍቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም መገልገያ አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡**

23. ስለጥብቅና አገልግሎት ውል እና ተያያዥ ግዴታዎች

1) **ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከሚሰጠው የህግ ምክር**

ayfaafayaak iroh maqmiil lih abah yan abookiini ayfaafayih ambalal kutbeh abam faxximta. Abookiini ayfaafayih ambalaalih addat haanam faxximtam egla miracsental madqele,

2) Abookiini ayfaafayih ambalal maqmiil abookeh mekla amolladi lakqo meklaay, elle meklan cogda kee waktiiy, abooke caagidil yaceeh yan abookiini ayfaafay elle daffeytam faxximta,

3) Faxe abooke akkek abookiini missoyna:-

A) Abookiini ayfaafay elle yacee biiroh kibiyyaay,

B) Abookiini taama yasgoorowe gitaak abe waanam kee

C) Abookiini ambalal xiiqe waa gaanuunsababah argaqe waanam kee abookiini ambalaalal qaddoysen mekla caddibnaak fuxxi ossotina mekla maqmiilil essere waanamih dirki le.

4) Ta maasayyak lani maasayyak 3(A) il wannottem anih, abookiini mihratih ayfaafayih roksat yacee xagar biro kibiyya xiqsisso abak esseram maxiiqa.

24. Anteemaniyya kee qadli wakliita yakkeenimi

1) Faxe abooke akkek abookiini missoyna abookiini ayfaafayih taama aamantiinol abaanam kee qadlih

አገልግሎት ውጭ ከደንበኛው ጋር የሚያደርገውን የጥብቅና አገልግሎት ውል በፅሑፍ ማድረግ አለበት፤ የጥብቅና አገልግሎት ውል ማካተት ስለሚገባቸው ነገሮች ማህበሩ በመመሪያ ይወስናል፤

2) **የጥብቅና አገልግሎት ዒሉ ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ የገንዘብ ክፍያ፤ የአከፋፈሉን ስልት እና ጊዜ፤ ጠበቃዉ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን የጥብቅና አገልግሎት የሚያካትት መሆን አለበት፤**

3) **ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-**

ሀ) ለጥብቅና አገልግሎት መስጫ የሚሆን ቢሮ የማሟላት፣

ለ) የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት ያለመስራት፣ እና

ሐ) የጥብቅና ውልን ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ያለማቋረጥ እና በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የክፍያ መጠን በላይ ተጨማሪ ክፍያ ከደንበኛ ያለመጠየቅ ግዴታ አለበት፤

4) **በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ሰጪው አካል ቢሮ ማሟላትን እንደመስፈርት ሊጠይቅ አይችልም፡፡**

24. <u>ስለታማኝነትና ለፍትህ አጋር መሆን</u>

1) **ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ስራውን በታማኝነት የመስራትና ለፍትህ አጋር**

waklenta yakkeenimih dirki keenil tan;

2) Ta maasayyak lani maasayyak (1) amolladi wano elle daccarsinte innal anuk, Faxe abooke akkek abookiini missoyna xiiqa sabab sinnim caagid agaaguluse wayaay, mingirwa diraabah massoyse wayaay, dirab alhumih xayyoyse way, xayyoyse kaliyyaay, biceenih xayyoowaanam kee faxxiimah yan gaarow abaanamaay, madqa rakiibno alle sinniih ayyaaqe sinni caagid abbixe waanamaay, maqmiil akke maqmiil sirrih ayyaaqe way kee kalah toobisle meqem kaban dirki kaal tan.

3) Gersi toobisluk abooke meqem kaban lih axaw le dirkitte biirooy, borxi akkek egla mablah racissol biro le gabuk biceh rakaakayak xiinisso malah buxa tayyaaqu wayta xintal madqimele.

Lani footimak nammaya

Madqah aydakaakan beyaanamih dirki

25. Hadaf

Madqah aydakaakanih hadaf rakaakayal abookiini roksat akah yeceen abokaato mihrat masquuliyatak akah yawqen innah ken xiqsissa qasri ixxiga kee dudda katayak akah yaallen innah ken xiqsiisaanam kinni.

26. Madqah aydakaakan wagsiisak

1) Faxe rakaakayal abookiini roksat akah yomcowwe abooke sanat addat

የመሆን ግዴታ አለበት፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን ያለማጓተት፣ ምስክሮችን በሐሰት ያለማደራጀት፣ ሀሰተኛ ማስረጃ ያለማቅረብ ወይም ያለማስቀረብ፣ ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ፤ የህግ መሰረት የሌለውንና የማያዋጣ ጉዳይን ያለመያዝ፤ የደንበኛውን ወይም ባለጉዳዩን ሚስጢር ያለማውጣት እና ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ግዴታ አለበት፤

3) ሌሎች መሰል ከጠበቃ ስነምግባር ጋር የተያያዙ ግዴታዎች በቢሮው ፣ በቦርዱ ወይም በማህበሩ ሀሳብ አመንጪነት በቢሮው በኩል ተዘጋጅቶ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

የሕግ ስልጠና የመውሰድ ግዴታ

25. ዓላማ

የሕግ ስልጠና ዓላማ የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀትና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው።

26. ስለ የሕግ ስልጠና

1) ማንኛውም የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ጠበቃ በዓመት ዉስጥ በድምሩ ከ24 እስከ 30 ሰአት የሚደርስ የሕግ ስልጠና የመውሰድ

sittat 24 ilaa 30 saaqat gufta madqah aydakaakan beyaamih dirki kaal tan;

2) Madqah aydakaakan sittallak leh akkek too sanatih addat kaah yaceenim xiqqimtah,

3) Madqah aydakaakan elle duudusan aydakaakan luuditteey, aydakaakan waktih xexxaaraay, amolladih aydaklaakan mattacok abni ekraarooy, aydakaakan mekla kee kalah aydakaakanat axaw le caagiida wagsiisak egla tayyaaqu wayta miracsental madqimele.

27. Mumaxxaga akah tomcowwe xisneena

1) Madqah aydakaakan taceem egla mumaxxaga akah tecee xisne akkele,

2) Abookiini missoynaani isinni gubat tan abookaatoh aydakaakan akah yaceen innah egla mumaxxagal keenih yaceenim xiqqimtah.

3) Egla abookiini missoynah akkek xisneh mamaxxaga yacee afal yaceen aydakaakan qaynatitte aakamal faatacisaanam faxximtaah, laakin aakamal faatacisen aydakaakan qaynatitte egla fooca fanah aysiisek, waasimek, hinnay duugumtam xiqtah.

4) Saittallak leh tan madqah aydakaakan tacayo mumaxxaga elle geyan siirat kee xiqissoosa wagsiisak egla tayyaaqu wayta miracsental madqimele

ግዴታ አለበት፤

2) **የህግ ስልጠናው በተከታታይ ወይም በዚያው ዓመት ውስጥ በተለያየ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፤**

3) **በሕግ ስልጠና የሚሸፈኑ የስልጠና ዘርፎችን፣ የስልጠና ጊዜውን ርዝመት፤ አጠቃላይ የስልጠና አሰጣጥ መርሃ-ግብር፤ የስልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከስልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።**

27. **<u>ዕውቅና ስለተሰጣቸው ተቋማት</u>**

1) **የህግ ስልጠና የሚሰጠው ማህበሩ እውቅና በሚሰጠው ተቋም ይሆናል፤**

2) **የጥብቅና ድርጅቶች በስራቸው ያሉ ጠበቆችን ስልጠና እንዲሰጡ በማህበሩ እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፣**

3) **ማህበሩ ለጥብቅና ድርጅት ወይም ለተቋም ዕዉቅና ከመስጠቱ በፊት የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶችን ቀድሞ ማፅደቅ ይኖርበታል፤ ሆኖም በቅድሚያ የጸደቁት የሥልጠና ዓይነቶች በማህበሩ ወደፊት ሊሻሻሉ፣ ሊታገዱ፣ ወይም ሊሠረዙ ይችላሉ፤**

4) **የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎች ዕውቅና የሚያገኙበት ሥነ ሥርዓት እና መሥፈርቶች በተመለከተ ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።**

28. Gabbaaqu abaanamih masquuliyata

1) Aydakaakan xisne aydakaakanal geytimta aydakaakanim aydakaakan edde qembiseeniih, tonnah aydakaakanak gaba kalte aydakaakanima, aydakaakanak gaba edde kalen waktiik qembisak yan inki alsa yakke waktih addat egla yaysixxigeenim faxximta;
2) axe abooke egla tiysixxige aydakaakan wakti aydakaanimuh kaa xiiqe kala xiiqa sabab akah yellek ta sabab egla kutbeh yaysixxigem faxximta.

29. Gaanuun/madqah aydakaakanih kattaate way

1) Faxe abooke ta lani footimal daffeyte madqah aydakaakanih dirki kibe kalah raaqe kaa tekkek egla tah biro kutbeh taysixxigem faxximta.
2) Biiro sittallak leh tan aydakaakan dirkit axawah anuk xiiqa sabab sinnim aydakaakan dirki beyam cine abookel ossobba malkit kaal ginaanam xiqqimtah.

30. Madqah aydakaakanih dirklh ayxeeriyya

1) Faxe abooke yayseemene sababah egla tayyaaqe aydakaakan waktih addat aydakaakan dirki beyam xiiqe week, abooke aydakaakan egla teyyeeqe waktih addat beyam xiiqe weem kee aydakaakan wakti akah kaah yayxeeren innah tatrusen aydakaakanih udduruk inki alsak afal aakamuk egla assabaltah yaysixxigem faxximta.
2) Abooke aydakaakan wakti akah kaah yayxeeren innah xayyoysa assabaltal, aydakaakan kaa bee kalah yan sababaay, aydakaakan beyuh abeh yan macal kee ciggiilak mawaqdi kee manni gurral beeleemil leh yan ekraaro

28. ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት

1) የስልጠና ተቋሙ በስልጠና ላይ ያሉትን ሰልጣኞች ስልጠና ከጀመሩበት እንዲሁም ስልጠና ያጠናቀቁ ሰልጣኞችን ስልጠናውን ካጠናቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፤

2) ማንኛዉም ጠበቃ ማህበሩ ባሳወቀው የስልጠና ጊዜ ለመሰልጠን የማያስችል በቂ ምክንያት ካለው ምክንያቱን ለማህበሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

29. የሕግ ስልጠና አለመከታተል

1) ማንኛዉም ጠበቃ በዚህ ንዑስ ክፍል የተቀመጡትን የሕግ ስልጠና ግዴታዎች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ማህበሩ ይህንኑ ለቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

2) ቢሮው ከተከታታይ የስልጠና ግዴታ ጋር ተያይዞ ያለበቂ ምክንያት የስልጠና ግዴታውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ባልሆነ ጠበቃ ላይ የድሲፕሊን ክስ ሊመሰርትበት ይችላል፡፡

30. የህግ ስልጠና ግዴታን ስለማራዘም

1) ማንኛውም ጠበቃ በአሳማኝ ምክንያት ማህበሩ በሚያወጣው የስልጠና ጊዜ ውስጥ የስልጠና ግዴታውን መውሰድ ካልቻለ ጠበቃው ስልጠናውን ማህበሩ ባወጣው ጊዜ ውስጥ መውሰድ ስላለመቻሉና የስልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት ማህበሩ ከያዘው የስልጠና ጊዜ ከአንድ ወር በፊት ቀድሞ ለማህበሩ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት

2) ጠበቃዉ የስልጠና ጊዜዉ እንዲራዘምለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ ስልጠናዉን መዉሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ ስልጠናዉን ለመዉሰድ ያደረገውን ጥረት፤ እና በቀጣይ መቼና በምን አግባብ እንደሚወስድ ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መሆን አለበት፤

qaddoysam faxximta.

3) Egla ta maasayyak lani maasayyak (2) amakkaquk keenil xayyowte assabalta tayseemeneemik sugtek, aydakaakan wakti too sanatih addat abooke essereh yan wakti akkek isinni keenit ceela wakti kaah milaagaanam xiqqimtah. Egla essero kaah oggoltek milaagi caalat hinnay essero kaak oggole weenik kaak oggole weenim 15 takke ayroorah addat kutbeh abooke yaysixxigeenim faxximta.

4) Abooke sanatat beyam kaak faxximta madqah aydakaakanih dirki addat akak yan sanatat amolladih beyam xiiqe weeh, aydakaakan akah bee weem kay duddak daga yekke sabab kinniimil alhum xayyoyse weeh, egla elle teemenek abooke bee weeh yan aydakaakan uddur ciggiila sanat fanah tabisak, ciggiila sanat beyam kaak qambalsima aydakaakan dirki lih dubleh akah beyan innah kaah idnisaanam xiqqimtah.

Lani maasayyak sidocu

Currik yan abookiini ayfaafayih dirki

31. Currik yan abookiini ayfaf yaceenimih dirki

1) Faxe abookiini missoynah addat agleh edde anek hinmnay tamlimeh taamita abooke akkek cankah taamita abooke caagid qilsak allinnaanih gide kee sahliinol amballayuk, sanatat sidiica caagidik fuxxite sinni currik yan abookiini ayfaafay yaceemih dirki kaal tan. Ayfaf akah yaceem:-

A. Meklaanamih dudda alle maraay;

B. Kira edde yaniinih hinnay elle sigan aracak madqa gitaak iroh duffuume marah,

C. HIV vayrisih sababah xaltani

3) ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የቀረበለት ማመልከቻ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የስልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ጠበቃው በጠየቀው ጊዜ ወይም እራሱ በመሰለው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል፤ ማህበሩ ጥያቄዉን ከተቀበለዉ የቅያሪውን ሁኔታ ወይም ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለው መሆኑን በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለጠበቃው ማሳወቅ አለበት፤

4) ጠበቃው በዓመት መውሰድ የሚጠበቅበትን የህግ ስልጠና ግዴታ በዚያው ዓመት አጠቃሎ መውሰድ ካልቻለ እና ስልጠናዉን ያልወሰደዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበና ማህበሩ ካመነበት ጠበቃው ያልወሰደውን የስልጠና ጊዜ ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የስልጠና ግዴታ ጋር ደርቦ እንዲወስድ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት

ስለ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ

31. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ

1) ማንኛዉም በጥብቅና ድርጅት ዉስጥ ሽሪክ ሆኖ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ጠበቃ፤ ወይም በግሉ የሚሰራ ጠበቃ እንደጉዳዩ ክብደት እና ቅለት እየታየ በዓመት 50 ሰዓት ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፤ አገልግሎቱ የሚሰጠዉም፡-

ሀ) የመክፈል አቅም ለሌላቸዉ ሰዎች፣

ለ) ከተከራዩበት ወይም ከሚኖሩበት ቦታ ከህግ አግባብ ውጭ ለተፈናቀለ ሰዎች፤

ሐ) በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት ወላጆቻቸውን አጥተው ለአካለመጠን ላልደረሱ ልጆች

wayteeh qumri akak gufe wee urru akkek ta dalkah sababah isinni xaylo wayteeh qumri akak warree xaltanih,

3) የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን አንድ አባል ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም፤
4) የቦርዱ ሰብሳቢ እና ጸሀፊ ከቦርዱ አባላት መካከል በአባላቱ ይመረጣል።

70. <u>የቦርዱ ስልጣን እና ተግባራት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) Egla beytah tan maaqattooti kee margaqooqiiy, tonnah kaadu egla tayyaaqeh tan miracsentitte kee kalah tan toobisle sanadittel madqâ lowsis aba;
2) Egla madaqta margaqooqil xayyowte weeqa hargaanamaay, kusaaqisaanam kee margaqa elle tatrusaanama;
3) Ta kuktak maasayyak 76(4) amakkaquk ossobba koboxuuy, maasayyak 78 amakkaquk abookiini mihratak culmah aqayyaareh makaadooy, tonnah maasayyak 80(1) amakkaquk abookiini roksatih agaaradih makaado tacee margaqal xayyowta weeqa hirigak fokkaaqak, margaqa elle yaceenimi.
4) Weeqa edde miraacisa uddur gitaliino le margaqa elle yacayoonuh cato takkeh axcuk yeemenek qusma alhum xayyoysiisak yable.
5) Ta maasayyak lani maasayyak 3 galab akak xaggiime makaado akkek qadli biiro hinnay koboxul gitah arcise weenih akkek kusaaqise ween lafa lem akkek alhum yenek caagid margaqa yecee xagar qagitak akah yable innah inki adda gaqitak miraacisaanama.
6) Abokaato kee abookiini missoyna yibbixeenih geytiman mihrat masquul;iyatak caabiino caddibna kee abookiini ayfaafayih meklah caddibna kee elle meklan siirat miracsental madqimele.

71. Burdi kutbeh buxa kee baajet wagsiisak,

1) Bordi biiroh addal kutbe buxa allele,
2) Bordi kutbeh buxah taama abeenit biiro le gabuk madabimelon, kutbe buxa abut wayta taamah rorta bordi

1) በማኅበሩ የሚወሰዱ ዕርምጃዎችና ዉሳኔዎች፤ እንዲሁም በማህበሩ በሚወጡ መመሪያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤
2) በማህበሩ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀበለው መመርመር እና ዉሳኔ መስጠት፤
3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76(4) መሰረት የዲሲፕሊን ጉባኤዉ፤ አንቀጽ 78 መሰረት የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴዉ፤ እንዲሁም በአንቀጽ 80(1) መሰረት የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብለው መመርመር፤ ዉሳኔ መስጠት፤
4) ቅሬታዉን በሚመረምርበት ወቅት ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ካመነ አዲስ ማስረጃ አስቀርቦ የማየት፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱት ኮሚቴዎች ወይም ፍትሕ ቢሮ ወይም ጉባኤዉ በአግባቡ ያላጣራዉ ወይም ያላጤነዉ ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ጉዳዩን ዉሳኔ ለሰጠዉ አካል በድጋሚ እንዲታይ ለአንድ ጊዜ መልሶ የመምራት፤
6) ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሊይዙት የሚገባውን የሙያ ኃላፊነት መድን መጠን፤ እና የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሥርዓትን በመመሪያ የመወሰን፡፡

71. <u>ስለቦርድ ጽህፈት ቤት እና በጀት</u>

1) ቦርዱ በቢሮው ዉስጥ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤
2) የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች በቢሮው

yayyaaqu waa miracsental madqimele.

3) Bordi adoytit bordi taama edde aban uddur keenih meklimtam faxximta mekla biiro keenih abele.
4) Bordik baajet xiinisso kee bordi adoytiitih mekla rorta biiro tayyaaqu wayta miracsental madqimele.

72. Bordi gex-gexsit kee margaqa

1) Bordi sanatat dagnal affara adda gaaboowele,
2) Ta maasayyak lani maasayyak 1 wano elle daccarsimte innal anuk, gaaboyse faxe uddur amokrada daffeynah seecam xiiqah,
3) Bordi adoytiitik madabiino taama biyaake sinniih, bordik taama agaaguluse sinni gurral gex-gexsit siirat akah baarimele,
4) Bordi adoytiitik dagnal konooy geytimek kobox kibbiimele;
5) Bordik margaqa elle yaceenim sittingey kinnuk, laakin sitta gey ane waa waqdi daffeynal yucdure adoytiitik fuxxi xongolo qokkolsimta wak kinni, xongolo inki gidel kurrumtek bordi gaaboyse qokle xongolo mayso allele,
6) Ta maasayyah wano elle daccarsimte innal anuk, bordi isi addah gex-gexsitih siirat wagsiisak ta kuktih wano sade la; miracsental

ይመደባለ፤ ጽህፈት ቤቱ የሚሰራዉ ስራ ዝርዝር ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፤

3) የቦርዱ አባላት የቦርዱን ስራ በሚፈፅሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በቢሮው ይሸፈናል፤
4) ስለቦርዱ በጀት አስተዳደርና ስለቦርድ አባላት ክፍያ ዝርዝሩ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

72. <u>የቦርድ አሰራር እና ውሳኔ</u>

1) ቦርዱ በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል፣
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰብሳቢው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
3) ቦርዱ የአባላቱን መደበኛ ስራ በማይጎዳና የቦርዱን ስራ በማይስተጓጎል መልኩ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
4) ከቦርዱ አባላት ቢያንስ አምስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
5) የቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በስምምነት ይሆናል ሆኖም ስምምነት ባልተገኘ ጊዜ በስብሰባዉ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፣
6) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የውስጥ አሰራር ስርዓት

madqaanam xiqqimtah.

73. Bordi margaqal xayyowta yoo maxiqta

Ta kuktak maasayyak 70 lani maasayyak (2) kee (3) amakkaquk bordi yacee margaqal dereemu haysite num yoo maxiqta margaqa edde yeexege ayrook xabba haanam 30 takke ayroorah addat rakaakayak fayyale cokmih buxal xayyoysam xiiqah.

74. Bordih miraacisan xisoosa

Ta kuktal xissimte abokaatok ossobba makaadoh koboxuy, abokiini mihratak culmah aqayyaare makaado kee abookiini roksatih agaaradih makaadok seecimeena bordi akkele.

75. Abokaatoh ossobbah koboxih xiso kee asaas.

1) Abookaatoh ossobbah kobox tahaak wider “koboxu” desitak seecimelem kee ta kuktal xissimte,

2) Kobox ciggilta xagortik edde angaluk kulli xisnek doorimak biro saqal ken reediselem kee addat 7 yakke adoytit allelon:-

A. Biirok nammay take awlisaay,

B. Abokaatoh eglak nammay take awlisaay,

C. Rakaakayak sangerra cokmih buxak inki awlise.

3) Inki adoytak taama daban namma sanat kinnuk, namma addaak fuxxi doorimam maxiiqa.

4) Kobox gaaboyse adoytit addak

በተመለከተ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሳይቃረን በመመሪያ ሊወሰን ይችላል።

73. በቦርዱ ዒሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በቦርዱ በሚሰጥ ዒሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ዒሳኔዉን ባወቀ በ30 ቀናት ዉስጥ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

74. በቦርዱ የሚመሩ አደረጃጀቶች

በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ፣ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል።

75. የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ መቋቋምና አወቃቀር

1) የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ ከዚህ በኋላ “ጉባኤው” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) ጉባኤው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡና በየተቋማቱ ተመርጠው በቢሮው ኃላፊ የሚሾሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከቢሮው ሁለት ተወካይ፣

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካይ፣

ሐ) ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ።

3) የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፤

kobox adoytit kaa doorele.

5) Kobox:-

A. Faxximte kaa tekkek faxe saaqat kobxaanam xiiqaanah,

B. Adoytiitik garabaak muxxi geytimek kobox kibbiimele,

C. Margaqooqi xongolo muxxul tatruse lon, laakin xongolo inki gide tekkek, gaaboyse qaxak tan xongolo kobboxuk margaqa akkele,

6) Ta maasayyak lani maasayyak 5 (A) —(C) wannowtem elle daccarsimte innal anuk, kobox isi daffeyna siiratih xinta tayyaaqem xiqtah.

76. Abookatoh ossobbah koboxih abbootan kee abtoota.

Koboxu:-

1) Abokaato kee abookiini missoynaanik taamah abnisso mihrat meqem kabanih xinta lih gexxam keeh kattaataanam elle xiiqan siirat baarimele.

2) Ta kukta akkek abookaatoh meqem kabanih xinta akkek miracsental taturak abooke kee abookiini missoynal xayyoowa malkit fokkaqtaah, malkit abooke akkek abookiini missoyna xayyoysissak waytam madaqta,

3) Malkit kee alhum abooke xayyoysissah axcuk madqeenik abooke raddi 30 ayroorah addat kutbeh akah xayyoysa innah seecisso kaah qaddoysak, malkit abookeh ruuban.

4) የጉባኤዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ ዉስጥ በጉባኤዉ አባላት ይመረጣል፤

5) ጉባኤዉ፡-

ሀ) እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፤

ለ) ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ) ዉሳኔዎችን በድምጽ ብልጫ ያሳልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ሲሆን በሰብሳቢዉ በኩል ያለዉ ድምጽ የጉባኤው ዉሳኔ ሆኖ ይጸድቃል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ከ(ሀ)-(ሐ) የተደነገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

76. <u>የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ስልጣን እና ተግባራት</u>

ጉባኤዉ፡-

1) የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም ከሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጠመ መሆኑን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

2) ይህንን አዋጅ ወይም የጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅት ላይ የሚቀርብ ክስን ይመረምራል፤ ክሱ ጠበቃዉን ወይም የጥብቅና ድርጅቱን የሚያስቀርብ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፤

3) ክሱ እና ማስረጃዉ ጠበቃዉን የሚያስቀርብ መሆኑን ከወሰነ ጠበቃዉ መልሱን በ30 ቀናት ዉስጥ በጽሁፍ እንዲያቀርብ በመጥሪያ ላይ

4) Abookel xayyoysen malkit kee alhum tonnah abooke le gabuk yomcowwe raddi kee alhum fokkaaqisak gaaroyseenik gamadal margaqa elle tatrusan.

5) Abookatoh meqem kabanih diddi elle maqqarowwaah, abookiini mihratih seemat edde dacrima caalat kusaaqisak bordil mabla xayyossa.

6) Faxximtam yablen wak ta kuktal yomcowwe ossobba malkit yableenimih abbootan rasu akkek daqaarak abookeh ossobbah makaadoh awlaytiinoh yaceenim xiiqaanah, awlaytiinok sabab qaddoysak kutbeh yaceenim faxximta.

77. Rasu akkek daqar abokaatok ossobba makaado

1) Makaado rakaakayak abookatok ossobba kobox awlaytiinoh tacee abooke akkek abookiini missoynak ossobba caagiid yabloonuh ciggilta adoytit allelon.:-

A) Rasuk qadli miracsenta akkek kutbe buixah saqal ---Gaaboyse

B) Abokaatoh egla awlisa namma awlaytit… Adoyta

C) Qadli miracsenta akkek ku/buxa awlissa inki awlise … Adoyta

D) Fayyale cokmih buxa awlissa inki awlise……Adoyta

2. Makaadok kutbe abe doorooy, inki adoytak taama daban kee koboxuk gex-

በመግለጽ ክሱን ለጠበቃዉ ይልካል፤

4) በጠበቃዉ ላይ የቀርበዉን ክስ እና ማስረጃ፤ እንዲሁም በጠበቃዉ በኩል የተሰጠ መልስ እና ማስረጃ ከመረመረ እና ካከራከረ በኋላ ዉሳኔ ይሰጣል፤

5) የጠበቆች ስነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን፤ የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

6) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን የድስፕሊን ክስ የማየት ስልጣን ለዞን ወይም ለወረዳ የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ውክልናውም ምክንያቱ ተገልጾ በጽሁፍ መሰጠት አለበት፤

77. የዞን ወይም የወረዳ የጠበቆች ዲስፕሊን ኮሚቴ

1) ኮሚቴው ከክልሉ የጠበቆች ድስፕሊን ጉባኤ በውክልና ለሚሰጠው የጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የድስፕሊን ጉዳይን ለማየት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የዞን ፍትህ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ ሃላፊ..... ሰብሳቢ

ለ) ከጠበቆች ማኅበር የሚወከሉ ሁለት ተወካዮች..... አባል

ሐ) ከፍትህ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ የሚወከል አንድ ተወካይ...አባል

መ) ከከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚወከል አንድ ተወካይ.....አባል

2) የኮሚቴው ጸሀፊ ምርጫ፣ የአንድ አባል

gexsit kee margaqa ta kuktal rakaakayak abokaatoh ossobbah koboxul elle wannotte innak amakkaquk akkele.

78. Abookiini mihratak culmah aqayyaareh makaadoh xiso kee asaas

1) Abokiini mihratak culmah aqayyaareh makaado tahaak wadir “aqayyaare makaado” axcuk muggaaqiomak ta kuktal xissimte.

2) Aqayyaare makaado ciggilta xagortik tewqeeh, ummaan xisnek doorinteeh, biiro saqal reedisa malciin takke adoytit allele:-

A. Biirok nammay takke awlisa,

B. Abokaatoh egla awlisa namma awlisa

C. Rakaakayak inayta magaalal geytimta rakaakayak fayyale cokmih buxak inki awlise

D. Rakaakayak inayta magaalal geytimta doolat jaamiqatak gaanuun barittoh buxak inki awlise

3) inki Aqayyaare makaadoh aadoytak taama daban namma sanat kinnuk, namma addaak fuxxi aqayyaare makaadoh adoytiinuh doorimaanam maxiiqan.

4) Aqayyaare makaadoh gaaboyse adoytit addak makaadoh adoytit kaa doorele,

5) Aqayyaare makaadoh daffeyna waksiisak:-

የሥራ ዘመን እና የጉባኤው አሰራርና ውሳኔ በዚህ አዋጅ ለክልሉ የጠበቆች ድስፕሊን ጉባኤ በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

78. <u>የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር</u>

1) የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ከዚህ በኋላ “የፈተና ኮሚቴ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የፈተና ኮሚቴው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ በየተቋማቱ የሚመረጡና በቢሮው ኃላፊ የሚሾሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከቢሮው ሁለት ተወካዮች፣

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካይ፣

ሐ) በክልሉ ዋና ከተማ ከሚገኝ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፣

መ) በክልሉ ዋና ከተማ ከሚገኝ የመንግስት ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት አንድ ተወካይ።

3) የአንድ የፈተና ኮሚቴ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በፈተና ኮሚቴ አባልነት ሊመረጥ አይችልም፤

4) የፈተና ኮሚቴዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ ውስጥ በኮሚቴው አባላት የሚመረጥ ይሆናል፤

5) የፈተና ኮሚቴዉን ስብሰባ በተመለከተ፡-

ሀ) ኮሚቴዉ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ

A. Makaado faxximtek faxe uddur gaaboowtam xiqtah.

B. Makaadoh adoytiitik garabaak daga geytimtek kobox kibbiimele.

C. Makaadok margaqa xongolo fuxxol tatrele, laakin xongolo inki gide tekkek gaaboyse xongolo muhimmat allele.

79. Makaadok abbootan kee adoota:-

Aqayyaare makaado:-

1) Biirok abookiini roksat tacee taama footima lih malloowak, dagnal sanatal namma adda abookiini duddak qeedaalissoh ayaqaare massoysak yekeereden uddur kee aracal yassaballih yaceen,

2) Aqayyaarek siirat kee wakti akah madqelon.

3) Aqayyaare waraakit asicciceeniih, elle taturan ximmo madqaanaah, xaloot qaduk yaysixxigen.

4) Aqayyaare arciinul gaba akak kale aqaare beeh aqayyaarel tatrem arcissa alhum kaah yaceen,

5) Aqayyaare siiratih xinta bicisak bordil xayyoyseenih faatacisan wak abinal asisan,

80. Makaadoh adoyitih assimah assenta

Makaadoh adoytit makaado taama edde aban uddur keenih meklintam faxximta mekla biro keenih duudusele.

81. Abokiini roksatih agaaradih makaadok xiso kee asaas

ሊሰበሰብ ይችላል፣

ለ) ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፣

ሐ) የኮሚቴዉ ዉሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝነት ይኖረዋል።

79. <u>የኮሚቴው ስልጣን እና ተግባራት፡-</u>

የፈተና ኮሚቴዉ፡-

1) በቢሮው የጥበቅና ፍቃድ ከሚሰጠው የስራ ክፍል ጋር በመመካከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የጥበቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፤

2) የፈተናውን ስነ-ስርአትና ጊዜ ይወስናል

3) የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ ይወስናል፤ ዉጤቱን በይፋ ያስታዉቃል፤

4) ፈተናዉን በስኬት ላጠናቀቀ ተፈታኝ ፈተናዉን ማለፉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል፤

5) የፈተና ስነ-ስርዐት ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ አቅርቦ ሲጸድቅ በስራ ላይ ያዉላል።

80. የኮሚቴው አባላት ውሎ አበል

የኮሚቴው አባላት የኮሚቴውን ሥራ በሚፈጸሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በቢሮው ይሸፈናል።

1) Tassaballoh abokiini roksat keenih yamcawwek faxximtak waytam madaqta abokiini roksatih agaaradih makaado ta kuktal xissimte.

2) Makaado ciggilta xagortik tewqeeh, kulli xisnek doorimak biiro saqal ken reedisa konooy takke adoytit allelon:-

A) Biirok nammay takke awlisa,

B) Abokaatoh eglak nammay takke awlisa nammay kee ,

C) Rakaakayak inayta magaalalal geytimta fayyale cokmih buxak inki Awlise

3) Inki Adoytak taama daban namma sanat kinnuk, namma addaak fuxxi aqayyaare makaadoh adoytiinuh doorimaanam maxiiqa.

4) Makaadok gaaboyse adoytit fanak biiro kaa muggaaqisele.

82. Abokiini roksatih agaaradih makaadoh abbootan kee abto

Makaado፡-

1) Yassaballi alhumitte fokkaaqak, yassaballih roksat akah yamcawwe innah hinnay kaah amcawwe wayuh madqan,

2) Yassaballi qadli taamah gexsit lih gexxa meqem kaban duddalem keeh arcisoonuh faxe num esserek hinnay alhum xayyoysiisak fokkaaqaanam xiiqaanah.

83. Abookiini roksatih agaaradih makaadoh daffeyna.

81. <u>የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር</u>

1) ለአመልካቾች የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው ስለመሆን አለመሆኑ የሚወስን የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

2) ኮሚቴዉ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ በየተቋማቱ ተመርጠው በቢሮው ኃላፊ ሚሾሙ አምስት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከቢሮው ሁለት ተወካዮች፣

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካዮች፣ እና

ሐ) በክልሉ ዋና ከተማ ከሚገኝ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፡፡

3) የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በአባልነት ሊመረጥ አይችልም፤

4) የኮሚቴዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በቢሮው ኃላፊ የሚሰየም ይሆናል፡፡

82. <u>የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴዉ ስልጣን እና ተግባር</u>

ኮሚቴው፡-

1) የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፍቃድ እንዲሰጠዉ ወይም አንዳይሰጠዉ ይወስናል፤

2) አመልካቹ ለፍትህ ስራ አካሂድ የሚስማማ የስነ-ምግባር ብቃት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛዉንም ሰዉ መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፡፡

1) Makaado faxximtem faxe uddur gaaboowaanam xiqaanah.

2) Makaadoh adoytiitik garabaak daga geytimtek kobox kibbiimah,

3) Makaado margaqooqi daffeynal geytime adoytiitik xongolo fuxxol tatrusan, takkay xongolo inki gidel kurrumtek gaaboyse muhimmik tan xongolo allele.

4) Ta maasayyal wannowtem elle daccarsimte innal anuk, makaado isinni daffeynah siiratih xinta yayyaaqeenim xiiqaanah.

Lani footimak sidocu

Biiro wagsiisak

84. Biirok abbootan kee abtoota

Biiro፡-

1) Abookiini roksatih agaaradih makaado abokiini roksat akah yamcawwuh akah madqen mihratlih abookiini roksat tacee.

2) Abokatoy, abokiini missoynaani kee aboke kee abokiini missoyna lih taamita mara taktubeeh, abookiini roksat taqusbuse.

3) Abokatok ossobba makaado elle madaqta innak amakkaquk abookiini roksat waassaah, duugtah.

4) Ta kuktak amakkaquk yawqu waa xintal elle madqan innak amakkaquk yaceenih yanin abookiini roksat kee gersi ayfaafayitteh meklaali gaabossa.

83. **የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴዉ ስብሰባ**

1) ኮሚቴዉ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

2) ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

3) የኮሚቴዉ ውሳኔዎች በስብሰባዉ በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

4) በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴዉ የራሱን የስብሰባ ስነስርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት
ስለ ቢሮው

84. **የቢሮው ስልጣንና ተግባራት**

ቢሮው፡-

1) የጥብቅና ፍቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ለወሰነለት ባለሙያ የጥብቅና ፍቃድ ይሰጣል ፤

2) ጠበቆችን፤ የጥብቅና ድርጅቶችን እና ከጠበቃ እና ከጥብቅና -ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ይመዘግባል፤ የጥብቅና ፍቃድ ያድሳል፤

3) የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ በሚወስነዉ መሰረት የጥብቅና ፍቃድ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

4) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ለሚሰጠው የጥብቅና

5) Abokato kee abokiini missoynaan tacee madqah ayfaafayitte bordi kee egla lih malloowak keexeena tayyaaqe,

6) Meqem kaban tatur lem tekke axcuk ascossi akak xayyoowe faxe abooke hinnay abokiini missoynal meqem kaban nakusi lem yugdubeenim keeh arcisoonuh fokkaaqo abtaah, ossobba malkit keenil qembissaah, gaarowtah,

7) Ta kukta kee ta kukta yagdaboonuh tawqu wayta xinta kee miracsentittel yeceenih yanin abbootan kee abtoota inki tanuuk akkek garabbih abookaatoh eglah awlaytiinoh tatrussam xiqtah,

8) Abookiini egla akah maqqarooway innah abak, baxaa-baxsale rakissoosa kee makaado akah xissiiman innah qokol abtaah, egla gersi xisneena lih gaanuun angaaraw elle ginan caaloota keenih sahhilossa.

9) Kukta yagdaboonuh egla kee bordi tayyaaqe miracsentitte massoysaanam kee akah faatacisan innah abak, tonnah amolladih abokiini ayfaafayitte wagsiisak egla akkek bordi hinnay kaadu gersi wagiitah yan xagorti ugussa qusba madqa akah tawqe innah akkek madqa maysaasa akah take innah faxsissa mabloolil gitaliinol madqa qagunta bicsaanam kee wagiitah yan xagarih

ፍቃድና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፤

5) በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ለሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች ከቦርዱ እና ከማህበሩ ጋር በመመካከር መለኪያዎችን ያወጣል፤

6) የስነ ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ በቀረበበት ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ላይ የስነ-ምግባር ጥሰቱ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ምርመራ ያካሂዳል፣ የዲስፕሊን ክስ ይመሰርታል፤ ይከራከራል፤

7) በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለጠበቆች ማህበር በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

8) የጥብቅና ማህበሩ እንዲጠናከር ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶች እና ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፤ ማህበሩ ከሌሎች ተቋማት ጋር ህጋዊ ግንኙነት ስለሚፈጠርበት ሁኔታ ያመቻቻል፤

9) አዋጁን ለማስፈጸም በማህበሩ እና በቦርዱ የሚወጡ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና እንዲጸድቁ በማድረግ፤ እንዲሁም አጠቃላይ የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ በማህበሩ፤ በቦርዱ ወይም ሌሎች በሚመለከታቸዉ አካላት የሚነሱ አዲስ ህግ እንዲወጣ ወይም የህግ ማሻሻያ እንዲደረግ በሚያስፈልጉ ሀሳቦች ላይ እንደአግባብነቱ የህግ ረቂቅ በማዘጋጀት እና በሚመለከተዉ አካል እንዲጸድቅ በማድረግ አስፈላጊዉን እገዛ

xaqul akah faatacisan innah abak faxxiimah yan cattiimiyya abta.

10) Egla barteh yan sahdayti caylak akah xissiima innah, ugtuma yakke baajet akah yallen inna kee xisne gurral yangayyeenim akah xiiqan innah faxxiimah yan qokol keenih abta.

11) Kalah ta kuktaay, ta kukta katayak yawqu waa xinta kee gersi gitaliino le madqooqil yeceenih yanin abbootan kee abtoota gexsissa.

Lecey-hayto footima

Ossobba qellatitte kee maaqattooti

Lani footimak tiya.

Sahlin ossobba qellat kee digaala

85. Sahlin ossobba qellatih qaynatitte

Ciggiltam kee too bis luk abokatoh meqem kabanih xintal wannowte abooke akkek abokiini missoyna bahta qelatitte sahlik tan ossobba qellatitte kinnon:-

1) Abookiini roksat maqmilwa akkek cokmi buxa hinnay wagiitah yan xagar akah yaybulle innah esseran wak yayballu ciniyya,,

2) Cokmi buxal akkek toobisle xisneenal mihrat wadaytu sadek, migaq kaak baysek hinnay gersi faxe gitah seebat kaak boolaysaanam gabbate yekkeenik,

3) Abooke awlise wee gaar abe matrah yan uddur abooke makkook tama

ያደርጋል፤

10)ማህበሩ በሰለጠነ የሰዉ ሀይል እንዲደራጅ፤ ለመነሻ የሚሆን በጀት እንዲኖረዉ እና እንደተቋም ለመንቀሳቀስ እንዲችል አስፈላጊዉን ድጋፍ ያደርጋል፤

11)ሌሎች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባራት ይፈጽማል፡፡

ክፍል ስድስት
የዲሲፕሊን ጥፋቶች እና እርምጃዎች
ንዑስ ክፍል አንድ
ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት እና ቅጣት

85. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት አይነቶች

የሚከተሉትና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የተደነገጉ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1) የጥብቅና ፍቃድን ለደንበኛ፤ለፍርድ ቤት ወይም ለሚመለከተዉ አካል እንዲያሳይ በተጠየቀ ጊዜ ለማየሳት ፈቃደኛ ያለመሆን፤

2) በፍርድ ቤት ወይም መሰል ተቋማት የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር፤

gaar abe kaa hoxissam xiqta abto lem baahanama.

4) Caagid edde yan caalat kee maadeh yan caddo maqmiil kaal essera wak gitah aysixxige way, maqmil butek hinnay seemat kaak xage yekkeenik,

5) Xiiqa waah ayseemene sinni sababah makkoh ayro ccokmi buxal geytime way,

6) Abokaatoh eglah meklam kaak qambalsinta mekla akkek ufya qagaa-qagitak, le waktil mekle waya,

7) Abookiini roksat le waktil aqusbuse way,

8) Aqusbuse ween abookiini roksatal abookiini ayfaafay yaceenimi.

9) Abookiini roksat abokiini roksat tacee xisnel gacise kalah gersi maytani taamal gaceenih geytimaanam.

86. Sahlin ossobbah qellatih digaala

1) Ta kuktak maasayyak 85 lani maasayyak (1) kee (2) wannotte qellatittek tiyaktaana kinni qellat baahe aboke hinnay abookiini missoynah afti maabitina ossobba koboxul yaceen, namma adda afti maabitina akah yaceen aboke akkek abokiini missoyna sidoc-haytoh adda toobisle qellat baahek kuktbe maabitina kaah tamcawwe.

2) Ta kuktak maasayyak 85 lani maasayyak (3) kee (4) wannotte qellatitte lem baahe abooke akkek

3) በጠበቃ ያልተወከለ ተከራካሪ ባጋጠመው ጊዜ ጠበቃው ሆን ብሎ ይህንኑ ተከራካሪ ወገን ሊያሳስቱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈጸም፤

4) ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታና የደረሰበትን ደረጃ በደንበኛው ሲጠየቅ በአግባቡ ያለማሳወቅ፣ ደንበኛን ማመናጨቅ ወይም ክብሩን መንካት፤

5) ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት ያለመገኘት፣

6) ለጠበቆች ማህበር መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ ወይም መዋጮ በተደጋጋሚ እና በወቅቱ ያለመክፈል፤

7) የጥብቅና ፍቃድን በወቅቱ አለማሳደስ፣

8) ባልታደሰ የጥብቅና ፈቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፡፡

9) የጥብቅና ፍቃዱን ለጥብቅና ፍቃድ ሰጭው ተቋም ሳይመልስ በሌላ ቋሚ ስራ ተሰማርቶ መገኘት፤

86. <u>የቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት</u>

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተደነጉ ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የቃል ማስጠንቀቂያ በዲሲፕሊን ጉባኤው ይሰጠዋል፤ ለሁለት ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠዉ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተደነጉትን ጥፋቶች የፈፀመ

abokiini missoyna kukbe maabitina keenih tamcawwe,

3) Ta kuktak maasayyak 83 lani maasayyak (5), (6), (7), (8) kee (9) wannotte qellatitte lem baahe abooke akkek abokiini missoyna caalat elle aninnaanih innal lakqo koona alfiik ilaa malcina alfih birri takke lakqo digaalah diggalsima.

Lani footimak nammaya

Qilsi ossobba qellatitte kee digaala

87. Qilsi ossobba qelatitte

Ciggiltam kee too bis luk abokatoh meqem kabanih xintal b axxaqimta abooke akkek abokiini missoyna bahta qelatitte qilsih tan ossobba qellatitte kinnon:-

1) Ta kuktak maasayyak 18(3) gubal roorinte taamoomi abooke cattiimiyyal hinnay madqa caagiidal kutbe abak tamlisak tamsiisaanam,
2) Isi gubal tamlise aboke cateyna kee qokol tacee taama abeenit roksat yacee xagar aysixxige way kee asqarre way,
3) Xiiqe waah ayseemene waa sababah mokko milaagu qagaa-qagitak esseraanam kee cokmi buxah caagid udurrusaanama,
4) Abookiini ayfaafayih mattacoh biiro akah alle kalah abokiini ayfaf

ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀፅ (5)፣ (6) (7)፣ (8) እና (9) የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር አምስት ሽ እስከ ብር ሰባት ሽ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት እና ቅጣት

87. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት አይነቶች

የሚከተሉት እና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የሚጠቀሱ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18(3) ስር የተዘረዘሩ ሰዎችን በጠበቃ ረዳትነት ወይም በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት መቅጠር እና ማሰራት፤
2) በስሩ የቀጠራቸውን የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ለፍቃድ ሰጭው አካል ያለማሳወቅና ያለማስመዝገብ፤
3) ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ መጠየቅና የፍርድ ቤት ጉዳይ እንዲጓተት ማድረግ፤

yaceenimi.

5) Madqal elle idnisen sababaak iroh sittallak leh dirki kinni madqah aydakaakan gitah bee waya,
6) Maqmilwak sirrih dacrise way,
7) Currik abokiini ayfaf akah yacee innah wagiitah yan xagar kaah miraacisa wak oggole cineh yenek,
8) Abokiini taama yasgoorowi gitaak abeh akkek gersi abokatoh asgooriwiyyi taama keenih abek,
9) Ta kuktak maasayyak 23(1) wannotteemiik sah maqmil lih aban abokiini ayfaafay ambalal sittingey kutbeh abe way,
10) Xiiqa sabab sinnim abokiini ambalal argaqek, hinnay abokiini ambalaalal baxxaqimte abokiini ayfaafayih meklat ossotinah maqmiil fayxiik iroh xiiqa sabab akah alle kalah ossotina mekla hirgek,
11) Ta kuktak maasayyak 33 galab akak xaggiime waktih addat insuransi caabiino cule kalah hinnay insuransi caabiino le waktil aqusbuse kalah abookiini ayfaafay yeceek,
12) Cokmi buxa akkek gersi margaqa yacee xagarih xaqul yablen caagiida wagsiisak gitaliino akke sinni gitah caagid margaqa akah geya innah abek,
13) Tuxxiq bood ugsek hinnay tuxxiq

4) የጥብቅና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤
5) በህግ ከተፈቀደው ምክንያት ውጭ ተከታታይ የግዴታ የህግ ስልጠና በአግባቡ አለመውሰድ፤
6) የደንበኛን ሚስጥር አለመጠበቅ፤
7) ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተዉ አካል ሲመራለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፤
8) የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት ወይም ለሌሎች ጠበቆች የአገናኝነት ስራ መስራት፤
9) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(1) ላይ ከተደነገገዉ በስተቀር ከደንበኛ ጋር የሚደረግ የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነትን በፅሁፍ ያለማድረግ፤
10) ያለበቂ ምክንያት የጥብቅና ውልን ማቋረጥ ወይም በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ከደንበኛው ፍላጎት ውጪ ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያ መቀበል፤
11) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ የመድን ዋስትና ሳይገባ ወይም የመድን ዋስትናው በወቅቱ ሳይታደስ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤
12) በፍርድ ቤት ወይም ሌሎች ውሳኔ በሚሰጡ አካላት ዘንድ ሚታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ አግባብ ባልሆነ መንገድ ውሳኔ ለማግኘት መጣር፣

bood le caagid kinnim aaxagih caagid gabat heek,

14) Kaah yomcowwe abokiini roksatih caddook daga abokiini ayfaf yeceek,

15) Maqmiil alhum alhum gitah cokmi buxal xayyoyswe weeh, duddaak addah gaaroowak maysaqarra xaloot baahe kaleh yenek,

16) Abokiini roksat faxe caalatal sidoc-haytoh exxa edde akah tantifiqe innah tatruseh yeceek,

17) Currik yan abokiini ayfaf yaceenim dirki kinnim aaxagih hinnay baaqid sinnah elle faxxinta innal akak awqe weeh, maqmiilik caagid akah finqita innah akkek xaloot akah baahe waa innah abaanama,

18) Ta kuktak maasayyak 35 kee 36(1), (4) kee (5) wannotte dirkittel taturak maqmiil amaanah cisaabih mabbux lih axaw le qellet lem baahek,

19) Saduh yan caagid lih aboke lih malisak hinnay alhum bayisak, maqmiil caagid xaloot akah baahe waa innah abek,

20) Madqa rakiibo alle sinniih, akak awqe wayu waam qqaduk akak tamixxige caagidik awqeyyo axcuk abbaxuk maqmiilik mekla higrek,

21) Dirab alhumut antifiquk hinnay faxe caalatal duquurusak abokiini roksat yeyyeeqek,

13)የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ወይም የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ መሆኑን እያወቀ ጉዳዩን መያዝ፤

14) ከተሰጠው የጥብቅና ፍቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

15)የደንበኛውን ማስረጃ በአግባቡ ለፍርድ ቤት አለማቅረብና ከአቅም በታች በመከራከር መዝገቡ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

16)የጥብቅና ፍቃድን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፤

17)ነፃ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታውን እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በአግባቡ ባለመወጣት የደንበኛን ጉዳይ እንዲበላሽ ወይም ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

18)በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 እና 36(1)፣(4) እና (5) የተደነገጉትን ግዴታዎች በመተላለፍ ከደንበኛ የአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን መፈፀም፤

19)ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ጋር በመመሳጠር ወይም ማስረጃ በማጥፋት የደንበኛ ጉዳይ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

20)የህግ መሰረት የሌለውንና እንደማያዋጣ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ያዋጣል በማለት መያዝና ከደንበኛ ክፍያ መቀበል፤

21) ሐሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ወይም

22) Abokiini mihratih ayfaafay lih axaw le xagni makooy, duquurisiyyaay, aylahisiyyaay, dirab sanad bicsek hinnay yoyfoofek, garqeeh toobis le meqem kaban nakusi lih axaw le baatilitteh cokmi buxal qellat li kaak axcuk akah diggalsimek,

23) Abookiini mihrat lih axaw tan dirab alhum xayyoyseh akkek akah xayyoysan innah abek, diram sumaq massoysak diraabah akah sumaaqitan innah , malkitime cokmi buxal akah xayyoowe waa innah akkek akah baya innah abekh hinnay faysek, saduh yan numuh cato yakke alhum edde akah antifiqe waa inah edde lowwitak baysaanam kee qadli akah makkoowa innah abaanam kee toobis luk meqem kaban nakusit axaw le baatilitteh cokmi buxal qellat kaak axcuk diggalsimek, ,

24) Waasinteh akkek duugen abokiini roksat waasimem hinnay duugumtem aaxagih abokiiini ayfaafay yaceenimi.

88. Qilsih yan ossobba qellatih digaala

1) Ta kuktak maasayyak 85 (3)-(6) fan tanih tan sahlin ossobba qellatitte sanatat namma addaak daga qellateena akkuk geytimeh akkek ta kuktak maasayyak 87 lani maasayyak (1) —(7) roorinte qellatittek tiyak teena yugdube aboke akkek abookiini missoyna birrik

በማንኛውም ሁኔታ በማታለል የጥብቅና ፍቃድ ማውጣት፤

22) **ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በእምነት ማጉደል፣ ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል፣ስርቆት፣ እና በመሳሰሉት ከስነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤**

23) **ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ሀሰተኛ ምስክር በማዘጋጀት በሀሰት ማስመስከር፣ተከሳሽ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ ወይም መምከር፣ ለተቃራኒ ወገን ጠቃሚ የሆነን ማስረጃ እንዳይጠቀምበት በማሰብ ማጥፋትና ፍትህ እንዲዛባ በማድረግ እና በመሳሰሉት ከስነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤**

24) **በታገደ ወይም በተሰረዘ የጥብቅና ፍቃድ መታገዱን ወይም መሰረዙን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፡፡**

88. <u>የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት</u>

1) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 85 **ከንዑስ አንቀጽ** (3) - (6) **ባለ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 87 **ከንዑስ አንቀጽ** (1) — (7) **ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሰባት ሺህ**

malcina alfii kee koona bool ilaa birrik taban kee koona alfih birri takke lakqo digaalah diggalsima.

2) Ta kuktak maasayyak 87 lani maasayyak (8) —(13) roorinte qelatittek tiyakteena lem baahe aboke akkek abnokiini missoyna birrik labaatanni alfiik ilaa birrik soddom alfi fan ntakke lakqo digaalah diggalsima.

3) Ta kuktak maasayyak 87 lani maasayyak (14) —(20) roorinte qelatittek tiyakteena lem baahe aboke akkek abnokiini missoyna caagid caalat elle aninnaanih innal ilaa laca alsa yakke waktih abokiini roksat akkek maysaqarra sumaaqih sertifikeet kaak waasinta.

4) Ta kuktak maasayyak 87 lani maasayyak (21) —(24) roorinte qelatittek tiyakteena lem baahe aboke akkek abnokiini missoyna abookiini missoyna abokiini roksat akkek maysaqarra sertifikeet kaak duugumta.

5) Ta maasayyak lani maasayyak 1 kee 2 galab akak xaggimte qellatitte lem baahak koona sanatih addat namma adda diggalsime aboke akkek abokiini missoyna gersi toobisle qilsi ossobba qellat baaheh yenek abookiini roksat akkek maysaqarra sertifikeet 6 alsaak ilaa 1 sanat fan yakke wakti kaak waasaanam xiqqimtah.

6) Ta maasayyak lani maasayyak 3

አምስት መቶ እስከ ብር አስራ አምስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

2) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 87 **ከንዑስ አንቀጽ** (8)-(13) **ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሃያ ሺህ እስከ ብር ሰላሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤**

3) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 87 **ከንዑስ አንቀጽ** (14)-(20) **ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ምስክር ሰርተፊኬቱ ይታገዳል፤**

4) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 87 **ከንዑስ አንቀጽ** (21)-(24) **ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፊኬቱ ይሰረዛል፤**

5) **በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ** 1 **እና** 2 **ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ፈጽሞ በአምስት አመት ጊዜ ዉስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ ከ**6 **ወር እስከ** 1 **አመት ለሚደርስ ጊዜ ሊታገድ ይችላል፤**

gubal galab akak xaggiime digaalak malcina sanatih addat namma adda diggilsime aboke akkek abokiini missoyna kalah toobnisle qilsi ossobba qellat baaheh geytimek abokiini roksat akkek maysaqarra sertifikeet kaak duugumele.

7) Ossobba qellatah qellat akkuk geytimaanam kee diggalsimaanam baatilih esserissa ossobba qellatitte wagsiisak baatil esserimiyyah maxayyoysa.

Lani maasayyak sidocu

Ossobba malkitih xayyoysiyyaay, wakti waadooy, yoo maxiqta kee baatil digaala.

89. Ossobba malkitih xayyoysiyya kee wakti waado

1) Ossobba malkitih xayyoysiyya kee gaarow siirat bordi yayyaaqu waa miracsental madqimele,

2) Sahlik yan ossobba qellatal xayyoowa malkit ossobba qellat abbinoowe udduruk qembisak inki sanatih addat xayyoowe weeh yenek wakti waadot waasimele.

3) Qisih yan ossobba qellatal xayyoowa malkit ossobba qellat edde yekke udduruk qembisak namma sanat yakke waktih addat xayyoowe week wakti waadot waasimele.

90. Yoo maxiqta wagsiisak:-

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የተጠቀሰዉን ቅጣት በሰባት አመት ውስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ የሚሰረዝ ይሆናል፤

7) በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት በወንጀል የሚያስጠይቁ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም።

ንዑስ ክፍል ሶስት

ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ይርጋ፣ ይግባኝ እና የወንጀል ቅጣት

89. ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ይርጋ

1) የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ እና የክርክር ስነስርአት ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

2) በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፤

3) በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።

1) Ossobba koboxih koboxih margaqal dereemu haysite num ossobba koboxih korraq kaa edde gute udduruuk soddom takke ayroorah addat bordil yoo maxiqta xayyoysam xiiqah.

2) Yoo maxiqta gaaroowih gexsit madabiino baatil yoo maxiqtah xayyoysiyyih siiratih gital mirracsimele.

3) Bordi margaqal dereemu haysite num madqa soxa le axcuk elle yeemenek bordi margaqa korraq kaa gufe udduruuk siddom takke ayroorah addat yoo maxiqta rakaakayak fayyale cokmih buxal xayyoysam xiiqah.

91. Baatil esserimiyya

Ta kuktak amakkaquk diggilsissa ossobba qellatitte baatil wanok lafalem kibta kaa tekkek, abooke akkek abookiini missoyna gitaliinmo le baatil madqal diggalsima.

Lani maasayyak fereey

Muggaaqisiyya

92. Muggaqisiyyi waytoh xayyoysiyya

1) Ta kukta kee kuktak amakkaquk tawqu wayta xintitte kee miracsentittek amakkaquk qilsi ossobba qellatah diggalsime aboke akkek abokiini missoyna qelatiini rikardi akah kaak duuguma inna kee migaq akah kaah gacisan innah esseram xiiqah.

2) Muggaaqisiyyi wayto elle xayyowtam ossobba kobox klinnuk,

90. **ስለ ይግባኝ**

1) በዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ግልባጭ በደረሰዉ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤

2) የይግባኝ ክርክር ሂደት በመደበኛው የወንጀል ይግባኝ አቀራረብ ስርዓት አግባብ ይመራል፤

3) በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የህግ ስህተት አለ ብሎ ካመነ የቦርዱ የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

91. **የወንጀል ተጠያቂነት**

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያስቀጡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የወንጀል ድንጋጌዎችን ፍሬ ነገሮች የሚያሟሉ ከሆነ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ አግባብ ባለዉ የወንጀል ህግ ይቀጣል።

ንዑስ ክፍል አራት

ስለ መሰየም

92. **የመሰየም አቤቱታ አቀራረብ**

1) በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኝነት ሪከርድ እንዲሰረዝለትና ስሙ እንዲመለስለት መጠየቅ ይችላል፤

wayto xayyowtam xiqtam digaalak gaba kalla heeh namma sanataak sarra kinni.

93. Muggaaqisiyyi siirat

1) Yassaballi kinni aboke akkek abokiini muggaaqisiyyi wayto ossobba koboxul xayyoysa.

2) Ossobba kobox faxximtaamak geytek biiroh akkek kalah wagiitah yan xagar waytol mabla akah yaceen innah abta.

3) Ossobba kobox biiro akkek wagiitah yan xagarih mabla oggolteeh yassaballi foocah yaabisak faxximta fokkaaqo abeeniik gamadal qellat rikardik akah duuguma innah madaqtam xiqtah.

94. Muggaaqisiyyi xalootitte

1) Yassubulle aboke akkek abokiini missyna qellatiini rikardi kaah duugumah.

2) Rikardi faxe qaynatih margaqal galab akak maxaggiima, roksat kaak duugumeh yenek caddol yaceenih yanin aqayyaare beeh tatreeh, ta kuktal galab akak xaggiime xiqissoosa kiba kaa tekkek roksat kaah yaduureh.

3) Ta maasayyak lani maasayyak (2) wano anih, ta kuktak maasayyak 87 (21)-(24) gubal wannowte qilsi ossobba qellatitteh sababah abookiini roksat akak duugumeeh hinnay tama abinittel baatilih diggalsimeeh, hinnay yaceeh yan abokiini ayfaafay lih axawah umaadoobi baatilih diggalsime hinnay makkook abeeh, tabna sanatih casbiik daga akah diggalsima baatilih qellatle axcuk diggalsime faxe aboke akkek abokiini

2) የመሰየም አቤቱታ የሚቀርበው ለዲሲፕሊን ጉባኤ ሆኖ አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው ቅጣቱን ከጨረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው።

93. <u>የመሰየም ሥርዓት</u>

1) አመልካች ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታውን ለዲሲፕሊን ጉባኤው ያቀርባል፤

2) የዲሲፕሊን ጉባኤውም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለቢሮው ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

3) የዲሲፕሊን ጉባኤውም የቢሮውን ወይም የሚመለከተውን አካል አስተያየት ከተቀበለና አመልካቹን በአካል በማነጋገር አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ጥፋቱ ከሪከርድ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል።

94. <u>የመሰየም ውጤቶች</u>

1) አመልካቹ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኝነት ሪከርድ ይሰረዝለታል፤

2) ሪከርዱ በማናቸውም አይነት ውሣኔ ላይ አይጠቀስም፤ ፍቃዱ ተሰርዞበት ከሆነ ለደረጃዉ የሚሰጠዉን ፈተና ተፈትኖ ካለፈ እና በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ፍቃዱ ይመለስለታል፤

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 87 (21) - (24) ስር በተደነገጉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ምክንያት የጥብቅና ፍቃዱ የተሰረዘበት ወይም በእነዚሁ ድርጊቶች በወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ከሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ታስቦ በሚፈጸም እና ከአስር ዓመት ጽኑ

missoyna muggaaqim te wakah, abookiini roksat kaah mayadaara, abokkiini ayfaafayih mihratal qagitak gacam maxiiqa.

95. Ossobba kobox tacee amriotte:-
Ossobba kobox inki abooke akah muggaaqima innah madqan wak, abooke kobox madaqtah gide takkem currik yan ayyunti ayfaafayaay tonnah kobox madaqta caagidiidah gid takkiinol currik madqah ayfaafay akah yacee innah amrissam xiqtah.

96. Abbonow waado
Muggaaqimiyya wagsiisak ta kuktih wanooni ta kukti yawqek afal qilsih yan ossobba qellatah diggalsimte abokaatol abbinow allele.

97. Muggaqsa kee sahlin qellatitte
Sahlin qellatah diggalsime aboke muggaaqisiyyi wayto xayyoysam kaak faxxiime kalah digaalak gaba edde kale udduruuk inki sanataak gamadal rikardi kaah duugan hinnay qafu kaah aban.

Malcin-hayto footima

Baxaa-baxsale wanooni

98. Xinta kee miracsenta yayyaaqeenimih abbootan
1) Rakaakayak xiinisso malah buxa ta kuktak yagdaboonuh xiqsiisah yan xinta tayyaaqem xiqtah.
2) Biirooy, bordi kee egla ta kuktal keenih yeceen abbootan kee abtoota yagdaboonuh ken xiqsissa miracsenta yayyaaqeenim xiiqaanah.

እስራት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የተሰየመ ቢሆንም የጥብቅና ፍቃዱ አይመለስለትም፣ በጥብቅና አገልግሎት ሙያ ድጋሚ መሰማራት አይችልም።

95. **የዲሲፕሊን ጉባኤው ስለሚሰጣቸው ትዕዛዞች**

የዲሲፕሊን ጉባኤው አንድ ጠበቃ እንዲሰየም ሲወስን ጠበቃው ጉባኤው ለሚወስነው ጊዜ ያህል ነፃ የማህበረሰብ አግልግሎት እንዲሁም ጉበኤው ለሚወስናቸው ጉዳዮች መጠን ያህል ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፤

96. **የተፈፃሚነት ወሰን**

መሰየምን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ለተቀጡ ጠበቆችም ተፈጻሚ ይሆናል፤

97. **መሰየምና ቀላል ጥፋቶች**

በቀላል ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልገው ቅጣቱን ከጨረሰ አንድ ዓመት በኋላ ሪከርዱ ይሰረዝለታል ወይም ቀሪ ይደረግለታል።

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

98. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

2) ቢሮው ፣ ቦርዱ እና ማህበሩ በዚህ አዋጅ

99. Tabaa-tabsi wanooni

1) Bordi kee egla ta kuktak amakkaquk keenih yeceen abtoo kee masquuliyat namma sanatih addat tabise lon.

2) Bordi kee egla isinni masquuliyat tabisaanam fanah biiro abokiini roksatih mattaco kee xiinisso taama bisoh heele.

3) Ta kuktak maasayyak 74 tescessime bordil seecimeena le abookiini mihratak culmah aqayyaareh makaado kee abokaatok ossobba koboxuk seecimeena egla ta masquuliyatitte tabsittuh duddalem bordi madqa wak, koona sanat yakke waktih addat nammay akkek nammayak tiyak-teeni egla fan tatrusa. Biiro egla tama masquuliyatittek gitah yewqeenim keeh kattaataah, faxximtam akak yublen maaqatta beyta, hinnay wagiitah yan xagar akah beya innah abta.

4) Ta kuktak mqasayyak 74 tescessime bordil seecimeena le abookini roksatih agaaradih makaado egla ta masquuliyatak yawquh libdo edde geyan uddur seecimeena keenik egla fan akah tabisan innah bordi faxe uddur madaqak tatrusam xiiqah.

5) Ta kuktak maasayyak 84(1) _ (4) il tescessime abtootah egla xissiimak,

የተሰጣቸዉን ስልጣን እና ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፤

99. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) ቦርዱ እና ማህበሩ በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጣቸዉን ተግባር እና ሀላፊነት በሁለት አመት ዉስጥ ይረከባሉ፤

2) ቦርዱ እና ማህበሩ ሀላፊነታቸዉን እስኪረከቡ ድረስ ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ስራን ይቀጥላል፤

3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 ላይ የተመለከቱትን ለቦርዱ ተጠሪ የሆኑትን የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ተጠሪነት ማህበሩ እነዚህ ሀላፊነቶች ለመረከብ ብቁ መሆኑን ቦርዱ ሲወስን በአምስት አመት ግዜ ዉስጥ ሁለቱንም ወይም ከሁለቱ አንዱን ወደ ማህበሩ ያስተላልፋል። ቢሮው ማህበሩ እነዚህን ሀላፊነቶች በአግባቡ ስለመወጣቱ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ነው ብሎ ያሰበውን እርምጃ ይወስዳል ወይም የሚመለከተው አካል እንዲወሰድ ያደርጋል፤

4) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 74 ላይ የተመለከተውን ለቦርዱ ተጠሪ የሆነውን የጥብቅና ፈቃድ ግምጋሚ ኮሚቴ ማህበሩ ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት ብቁ በሚሆንበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለማህበሩ እንዲተላለፍ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ

masquuliyat tabisam xiiqam biiro arcissah tan wak, masquuliyatittel inkih akkek yekeeredeenimih miracsenta ayyaaquk egla fan tatrussam xiqtah. Biiro tama masquuliyatitte tatrussek gamadal gitah tekkeh tanim kattaataanam kee oxiit abaanamaay, tonnah faxximtanm yablen wak faxximta maaqatta beek hinnay akah beyan innah abaanamih masquuliyat le.

6) Ta kukti abinal asak afal mabnulul akak yanin caagiida ta madqal taamal assaamak afal diggowteh sugte madqooqik amakkaquk margaqa geele.

7) Ta kukti diggoowak afal yeceenih yanin abokiini roksatitte elle faxxiiminnaan innal ta kuktak amakkaquk roksat yamcawwe mara kee yaqusbuseenim faxximtam elle daccarsimte innal anuk abinal aselon.

100. Duugum-teeh abinal ase wayta madqooqi

1) Rakaakay cokmih buxaaxil taamitta abokatoh roksat mattaco kee maysaqarra xintih ixximak 6/1996 wannotte gersi wanooni ta kuktal duugumteh.

2) Ta kukta sadda faxe kuktaay, xintaay, miracsenta akkek gex-gexsit ta kuktal duudumte caagiidal abbinos mayalla.

ሊወስንና ሊያስተላልፍ ይችላል፣

5) **በዚህ አዋጅ አንቀጽ** 84 (1)-(4) **ላይ የተመለከቱ ተግባራት ማህበሩ ተደራጅቶ እና ሀላፊነቶቹን መረከብ እንደሚችል ቢሮው ሲያረጋግጥ ሀላፊነቶቹን ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን መመሪያ በማውጣት ወደ ማህበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል። ቢሮው እነዚህን ሀላፊነቶችን ካስተላለፈ በኋላ ተግባራቱ በአግባቡ ስለመፈጸማቸዉ መከታተል እና አዲት የማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፣**

6) **ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ይህ ሕግ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተው በነበሩት ህጎች መሠረት ውሣኔ ያገኛሉ፤**

7) **ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተሰጡ የጥብቅና ፈቃዶች እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ መሰረት ፍቃድ የሚሰጣቸውና መታደስ ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የፀኑ ናቸው።**

100. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1) **በክልሉ ፍ/ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ ደንብ ቁጥር** 6/1996 **የተደነገጉ ሌሎች ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሸረዋል።**

2) **ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሰራር**

101. Kukti abinal edde asu waa uddur

Ta kukti rakaakayak xinkaara maybalaalaqal yitbiqqimeh edde yawqu waa ayrook qembisak abinal asele.

Samara -----ayro 2018 I.L.L

Awwal Qarba Qunxe

Qafar Agatih Rakaakayih Doolatak

Xiinissoh abba

በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

101. <u>አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ዲንካራ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሰመራ፣ ታህሳስ 30 ቀን 2018 ዓ.ም

አወል አርባ ዑንዴ

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ-መስተዳድር